አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት

የድኅረምረቃ መርሃግብር

# ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፤ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በደገሉ ሮቢ

የጥናቱ አማካሪ:- ዳዊት ፍሬሕይወት (ዶ/ር)

መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፤ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ
የዐማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት
የድኅረ ምረቃ መርሃግብር

አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለትምህርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ
የቀረበ ጥናት

በደገሉ ሮቢ

መስከረም 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የዐማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት

## የድኅረ ምረቃ መርሃግብር

“ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፤ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በደገሉ ሮቢ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ-----------------------------------------ፊርማ-----------------------ቀን----------------------

የውስጥ ፈታኝ-------------------------------ፊርማ-----------------------ቀን---------------------

የውጭ ፈታኝ--------------------------------ፊርማ------------------------ቀን--------------------

# የአጥኚው ማረጋገጫ

“ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ፤ በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያነት በደገሉ ሮቢ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ የዐማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለትምህርት የድኅረ ምረቃ መርሃግብር ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት  ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል በዚህ ትምህርት ቤት ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኳቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና የተጠቀሱ በመሆናቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም-----------------------------------------

ፊርማ--------------------------------------

ቀን-----------------------------------------

# ምስጋና

በመጀመሪያ ምህርቱና ቸርነቱ ከእኔ ላልተለየኝና ለዚህ ፍጻሜ ላበቃኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው፡፡ በመቀጠል ይህንን ጥናት ሳካሂድ ተገቢውን ምክር በመለገስ ከትልመ-ጥናቱ እስከ ዋናው ጥናት ሂደት መጨረሻ ድረስ ሀሳብ በመስጠት እና በመገምገም ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ጥናቱን በተገቢው ሁኔታ እንድሰራ በማድረግ ለውጤት ላበቁኝ ለአማካሪዬና መምህሬ ዳዊት ፍሬሕይወት (ዶ/ር) ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡
እንዲሁም ይህ ጥናት በተገቢው መንገድ ይሰራ ዘንድ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለኦዳ ቢስል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተዳደር፣ መምህራንና ለትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በተለይ በጥናቱ ቀጥተኛ ተሳታፊ ለነበሩ ተማሪዎች ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡

በመጨረሻም ድጋፋቸውን፣ ሀሳባቸውን፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ በመስጠት ለዚህ ጥናት መሳካት ከፍተኛ የሆነ እገዛ ላደረጉልኝ ውድ ባለቤቴና ቤተሰቦቼ ትልቅ ክብር አለኝ ፡፡

# አኅጽሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ አላማውን ከግብ ለማድረስም ተዛምዷዊ የጥናት ስልት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን በእሉ ገላን ወረዳ ከሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የኦዳ ብሲል ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይህ ትምህርት ቤት አመቺ የንሞና ዘዴ በመጠቀም ተመርጧል፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓ.ም በአምስት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ተማሪዎች ተመድበው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሲሆን ከአምስቱ ምድብ (ክፍል) ውስጥ 10ኛ “D” የመማሪያ ክፍል ተማሪዎችን በቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴ ተወስደው በአጠቃላይ 80 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ከጥናቱ ተሳታፊዎችም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃም በአማካይ ውጤት፣ በመደበኛ ልይይትና በፒርሰን የተዛምዶ ስሌት ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተውም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ በመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ አዎንታዊ እንደሆነ አመላክቷል፡፡ የተዛምዶው መጠንም ጭንቀትን መቀነስ ($r = 0.846$, $p = .001$) ሲሆን ጥያቄ መጠየቅ($r = 0.642$, $p = .001$) ሆኖ ተገኝቷል፤ በትብብር መስራት ($r = 0.701$, $p = .001$) መሆኑን አሳይቷል፡፡ ጭንቀትን መቀነስ፣ ጥያቄ መጠየቅና በትብብር መስራት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያላቸው የተጋርቶ መጠንም $R2 = 0.521$ ወይም 52.1% ነው፡፡ ይህም የሚያመላክተው የተማሪዎች ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ $R2 = 0.521$ በመሆን ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ አለ ከሚለው ድምዳሜ ላይ ተደርሷል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ መምህራን ማንበብን በሚያስተምሩበት ወቅት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ቢያስተምሩ ተመራጭ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ይህ ርዕሰ ጉዳይ አዎንታዊ እንዲሆን የሚያደርጉ ስራዎች በሌሎች ተለውጦዎች፤በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ላይ በርከት ባሉ ናሙናዎች ወደፊት ቢፈተሹ ከዚህ የተሸለ ውጤት ሊገኝ ይችላል የሚል ሃሳብ ተመላክቷል፡፡

# ማውጫ

**የይዘት ዝርዝር** **ገጽ**


ምስጋና .................... i
አኅጽሮተ ጥናት .................... ii
ማውጫ .................... iii
የሰንጠረዥ ማውጫ .................... v
ምዕራፍ አንድ .................... 1
መግቢያ .................... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ .................... 1
1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር .................... 4
1.3 የጥናቱ ዋና ዓላማ .................... 9
1.3.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ .................... 9
1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ .................... 9
1.5. የጥናቱ ወሰን .................... 10
1.6 የጥናቱ ውስንነት .................... 10
1.7.1. ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት .................... 11
1.7.2. አንብቦ የመረዳት ችሎታ .................... 11
1.7.3. የማንበብ ተነሳሽነት ብልሃት .................... 11
ምዕራፍ ሁለት .................... 12
ክለሳ ድርሳናት .................... 12
2.1 የቋንቋ መማር ብልሀቶች ምንነት .................... 12
2.2 የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ምንነት .................... 14
2.3 የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ክፍሎች .................... 16
2.3.1 ጭንቀትን መቀነስ .................... 16
2.3.2 ጥያቄ መጠየቅ .................... 17
2.3.3 በትብብር መስራት .................... 17
2.5 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምንነት .................... 18
2.4 ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው .................... 19
ተዛምዶ .................... 19
ምዕራፍ ሶስት .................... 20

የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ...............................................................................................20
3.1 የጥናቱ ንድፍ ...............................................................................................20
3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ ...............................................................................20
3.3.1 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ...............................................................................21
3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ ...............................................................................21
3.4 የአጠናን ሂደት ...............................................................................................22
3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ...............................................................................................23
ምዕራፍ አራት ...............................................................................................24
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ...............................................................................24
4.1 የመረጃ ትንተና ...............................................................................................24
4.2 የውጤት ማብራሪያ ...............................................................................................27
ምዕራፍ አምስት ...............................................................................................28
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት ...............................................................................28
5.1 ማጠቃለያ ...............................................................................................28
5.2 መደምደሚያ ...............................................................................................29
5.3 አስተያየት ...............................................................................................30
ዋቢዎች ...............................................................................................32
አባሪዎች ...............................................................................................36
አባሪ ሀ. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ...............................................................................36
አባሪ (ለ). የጽሑፍ መጠይቅ ...............................................................................41
አባሪ ሐ. የሙከራ ጥናቱ (Pilot Study) አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ...............................................................................43
አባሪ መ. የሙከራው ጥናት (Pilot Study) የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ...............................................................................44
አባሪ ሠ. የዋናው ጥናት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ...............................................................................45
አባሪ ረ. የዋናው ጥናት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት ...............................................................................47
አባሪ ሰ. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት አስተማማኝነት ...............................................................................49
አባሪ ሸ. የጽሑፍ መጠይቁ ውጤት አስተማማኝነት ...............................................................................49
አባሪ ቀ. ከአንብቦ መረዳት ችሎታ የተገኘ የስታትስቲክስ ስሌት ውጤት ...............................................................................49
አባሪ ተ. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ የስታትስቲክስ ስሌት ውጤት ...............................................................................50
አባሪቸ. ከአንብቦ መረዳት ችሎታ የተገኘ የስታትስቲክ ስሌት ውጤት ..51
አባሪ ኀ. የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ተዛምዶ በስታትስቲክ ስሌት 51

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ፤4.1 የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በፒርሰን ተዛምዶ የመወሰኛ ቀመር ........ 24

ሰንጠረዥ፤ 4.2 ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻና ደረጃ በድኅረታዊ ትንተና ........ 25

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

ማንበብ የሰው ልጆች የዕለት ከዕለት ህይወታቸውንና የመማር ሂደቶቻቸውን ሊያሳልጡበት የሚችሉት ክሂል ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ማንበብ ሰዎች የተለያዩ መረጃዎችን የሚያገኙበት፣ የተገኙ መረጃዎችን የሚያብራሩበት፣ የሚተረጉሙበትና ግንዛቤ የሚጨብጡበት ተግባር ነው (Grebe & Stoller, 2002)፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ተግባር እጅግ ውስብስብ የሆኑ ሂደቶችን የሚያልፍ በመሆኑ አንባቢያን አዕምሯዊ፣ ልዕለ-አዕምሯዊ፣ ተነሳሽነትንና ማህበረ አዕምሯዊ ብልሃቶችን በጥምረት አቀናጅቶ ተግባራዊ ማድረግን ይጠይቃል (Grebe& Stoller, 2002)፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታ አዕምሯዊ ሂደት በመሆኑ የተለያዩ ተግባራትን በጥምረት ማከናወን ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም አንብቦ የመረዳት ችሎታ ትኩረት ማድረግን፣ ማስታወስን፣ የመተንተን ችሎታን፣ የመተርጎም ችሎታንና የመመሰል አቅምን ይፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንባቢያን የራሳቸውን የመገንዘብ ሂደት ማወቅ መቻል አለባቸው (Baker & Brown, 1984)፡፡ በመሆኑም አንባቢያን የተለያዩ የመማር ብልሃቶችን ተግባራዊ ማድረግ ሲችሉና የመረዳት ሂደታቸውን መገንዘባቸውን ሲያውቁ አንድን ምንባብ አንብበው የመረዳትና ትርጉም የመስጠት ችሎታቸው ከፍ ይላል (Pears & Paris, 2008)፡፡

አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች ስልታዊ የሆኑ ተግባራትና ባህርያት ወይም ደግሞ ልምዶች ሲሆኑ ተማሪዎች የአንድን ምንባብ ቅርፅ፣ ይዘትና አቀራረብ እንዲረዱ ያስችላሉ (Sabatini, Bruce& Steinberg, 2013)፡፡ እንደ Haker (2009) ደግሞ አንብቦ የመረዳት ብልሃቶችን ተማሪዎች ማንበብ ከመጀመራቸው በፊት፣ በሚያነቡበት ጊዜና ከአነበቡ በኋላ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ሲሆን መረጃውን ለመተንተን፣ ለማደራጀትና ትርጉም ለመስጠትያለው ብልሃት አንብቦ የመረዳት ሂደትን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህ መሰረትም አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች ተማሪዎች አንድን ምንባብ አንብበው ለመረዳት የሚያስችላቸውን ሂደትና ተግባራት በትክክል እንዲተገብሩ በማድረግ መንገዱን እንዲያስተካክሉ ለማድረግ ያስችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ተማሪዎች በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የራሳቸውን የመማር ስልት መምረጥ፣ እንዲሁም የመማር ብልሃቶችን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ መማር ብልሃቶች በተማሪዎች የቋንቋ መማር ሂደትና አጠቃቀም ላይ የራሳቸው የሆነ አዎንታዊ ተፅዕኖ ስላላቸው ነው (Sheng, 2008)፡፡ Liwos & Dorling(1999) እንደሚሉት በተማሪዎች መካከል የባህርይ፣ የማህበራዊና ባህላዊ ዳራ፣ የዕድሜና የመማር ምርጫ ልዩነቶች አሉ፡፡ በመሆኑም ቋንቋን በመማር ሂደት ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ስብዕናዊ፣ አዕምሯዊ፣ አመለካከታዊ፣ ዝንባሌያዊ፣ ግብዓታዊና ግላዊ የመማር ማስተማር ስልትና ብልሃት ምርጫዎች አሉ (Richards,1990)፡፡

ተማሪዎች ቋንቋን በመደበኛው መርሃግብር ለመማር ሲመጡ በቋንቋ ትምህርታቸው ላይ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ የሆኑ ተፅዕኖዎች ማሳደር የሚችሉ የየራሳቸው ግላዊ ባህርይ፣ ችሎታ፣ የመማር ብልሃትና ግብ ይዘው ነው (Richards,1990)፡፡ Stern,(1983) በበኩላቸው በተማሪዎች መካከል የመማር ብልሃት ምርጫ ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ባላቸው የተሰጥኦ ችሎታ ልዩነት፣ ለመማር ባላቸው ፈቃደኝነትና በመማር ብልሃቶች ምርጫ ይለያያሉ፡፡

ከሃያኛው ክፍለዘመን አጋማሽ ጀምሮ  እስካሁን ድረስ ባሉት አመታት የመማር ብልሃትንና አንብቦ መረዳትን በሚመለከት የተለያዩ የማንበብ ንድፈሃሳቦች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ ንድፈሃሳቦቹ ተማሪዎች በባህርይ፣ በተፈጥሮ፣ በአካባቢ ልዩነት በመኖሪያ ቤትና በትምህርት ቤት ተፅዕኖ ምክንያት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን የመማር ብልሃታቸው እንዴት ሊያጎለብት እንደሚችል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

ሆኖም ግን የቋንቋ መማር ብልሃቶችን በተመለከተ በብዛት ምርምር ማድረግ የተጀመረው በ1960ዎቹ አካባቢ ነው፡፡ ይህም ከአዕምሯዊ ስነ-ባህርይ እድገት ጋር ተያይዞ የመጣ ነው (Williams & Burden,1997)፡፡ እንደ Pintrich & Digrut (1990) የተለያዩ የምርምር ስራዎችን መሰረት በማድረግ እንደሚገልፁት ሶስት የመማር ብልሃት አይነቶች የተቀረፁ ሲሆን እነሱም አዕምሯዊ፣ የማስታወስና ራስመር ብልሃቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል Brown (1994) የRubin (1987)ን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ተማሪዎች በቋንቋ መማር ወቅት የሚጠቀሙባቸው ሶስት አይነት ብልሃቶች አሉ፡፡ እነሱም ተግባቦታዊ ብልሃቶች፣ የመማር ብልሃቶችና ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ማህበረ-

ስሜታዊ ብልሃቶችን መማር ወይም ማወቅ አንድ ሰው ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር፣ አብሮ በመስራት አንብቦ ለመረዳት ችሎታው መዳበር መሰረት የሚጥልበት ነው፡፡

እንደ Rubin (1987) ገለፃ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች ስለሚማሩት ትምህርት ያላቸውን ስሜት በመረዳት፣ በመጠየቅ፣ ስሜታቸውን ተቆጣጥረው አብሮ በመስራት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በሌላ በኩል ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት የመተባበርና ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃት ሲሆን ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር ተረዳድተው በመስራትና ግብረ መልስ በመቀበል የመማር ሂደታቸውን ያሳልጡበታል፤ ከቋንቋው ባለቤቶች ጋር ይበልጥ ለመቀራረብ የሚሞክሩበት እንዲሁም የታላሚውን ቋንቋ ባለቤቶች ደንብ ለማወቅ የሚጠይቁበት ብልሃት ነው (O’Malley & Chamot, 1985)፡፡

ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት ተግባራዊ እየሆነና እጅጉን እየታወቀ የመጣው ከ1980ዎቹ ወዲህ ሲሆን የዚህ ብልሃት አመንጪዎችም ኦማሌና ቻሞት እንደሆኑ(Vijaya 2012) ይገልፃሉ፡፡ ይህ ብልሃት የመማር ብልሃት በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት በተማሪዎችና በመምህራን መካከል ያለውን የመተሳሰብ፣ ችግርን የመጋራት፣ ስሜትን የመረዳት ብልሃት ነው (Oxford, 1990)፡፡ እንደ Zadih(2008) ገለፃ ደግሞ ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት በተማሪዎች ስሜት ላይ የሚያተኩር ሲሆን ከቋንቋው መማር ጋር የሚዛመዱ ውስጣዊ ስሜቶችን፣ መነሳሳቶችን፣ ፍላጎቶችንና ጭንቀቶችን ለመቆጣጠር የሚያግዝ ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ የመማር ሂደትን በተማሪዎችና በመምህራን እንዲሁም በተማሪዎችና በተማሪዎች መካከል መስተጋብር በመፍጠር ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ በትብበር መስራትንና ስለሌሎች ሰዎች ሀሳብና ስሜት መፍጠርን የሚመለከት ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃቶችን ተግባራዊ በማድረግ ቋንቋን ሲማሩ የሚፈጠርባቸውን እጅግ የናረ ጉጉት፣ ፍርሃት፣ ጭንቀት፣ አለመረጋጋትና ቁጡነት መቆጣጠር ይችላሉ (Oxford፣ 1990)፡፡

ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት የተማሪዎችን የእርስ በርስ ተራክቦ የሚያፋጥን ስለሆነ በመካከላቸው የቤተሰባዊነትና የጓደኝነትን መንፈስ ስለሚፈጥር ለቋንቋው መማር አዎንታዊ ድርሻ ይኖረዋል (Brown, 2002)፡፡ በሌላ በኩል እንደ Oxford (1990) ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን ስሜት፣ ዝንባሌ፣ ተነሳሽነትና መነቃቃት ጋር እጅግ የተቆራኘ ነው፡፡ ተማሪዎች በመማር ሂደታቸው ወቅት የሚፈጠርባቸውን አሉታዊ

ስሜት መቆጣጠር እንዳለባቸው ይረዳሉ፤ ጥሩ ያልሆነ ስሜት ሊፈጥርባቸው የሚችለውን ለውጥ ይቀለብሳሉ፤ መልካም የሆነ ስሜት ደግሞ የመማር ሂደታቸውን አስደሳች እንዲሆን ያደርጋል። ይሁን እንጂ ይህን አልፎ ተማሪዎች የመማር ሂደታቸውን ችግር ውስጥ የሚከት ስሜት ሲሰማቸው የተፈጠረውን ነገር እንዳልተፈጠረ መውሰድ፣ ስህተትን መቀበል፣ አዎንታዊ የሆነ ሃሳብ ማመንጨት እና ራስን ለማበረታታት መሞከር ተገቢ ነው። እንደ O'Malley & Chamot, (1990) ገለፃ በቋንቋ መማር ሂደት ጥሩ ያልሆነ ስሜት ሲፈጠር መቆጣጠር የሚቻለው ከጓደኛ ጋር በመወያየት (ሀሳብን በመጋራት)፣ አዎንታዊ የሆነ መስተጋብር በመፍጠር፣ ያልተረዱትን በመጠየቅ፣ ከራስ ጋር በመነጋገርና ራስን በማበረታታት ነው ።

ከላይ ከተነሱት ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ከጓደኞቻቸው ጋር እየተጋገዙ እንዲሰሩ፣ ግልፅነት የጎደላቸውን ተግባራት የተሻለ የተረዱ ተማሪዎችን፣ መምህራንንና በዙሪያቸው ያሉ አካላትን በመጠየቅ እንዲረዱ የሚያስችል ብልሃት እንደሆነ ነው። ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባራትም ከአቻዎቻቸው ጋር ህብረት መፍጠር፣ ከእነሱ የተሻሉ እንደሆኑ ከሚያስቧቸው ሰዎች እገዛ ለማግኘት መቀራረብ፣ ስህተት ተቀብሎ ማስተካከልና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሲማሩ ከሌሎች ሰዎች ጋር አዎንታዊ የሆነ መስተጋብር በመፍጠር ተጋግዘው የሚማሩ ከሆነ የመረዳት ችሎታቸውም የተሳለጠ ይሆናል።

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

ማንበብ የአንድን ፅሁፍ መልዕክት መረዳትንና መተርጎምን የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባር በመሆኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት መምህራን ለተማሪዎቻቸው አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ብልሃቶችን ማስተማር ይጠበቅባቸዋል (Aebersold & Field,1997)። ይሁን እንጂ ባሁኑ ወቅት ተማሪዎች ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት የላቸውም። ተማሪዎች በትምህርት አለም እያሉ በየዕለቱ ከሚነበቡ በርካታ ፅሁፎች ጋር ይገናኛሉ። ሆኖም ግን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው በአግባቡ ከፅሁፎች ተገቢውን እውቀት ለመቅሰም አያስችላቸውም (Graham, 1987)። እንደAtkins & Others (1996) በበኩላቸው ተማሪዎች የዳበረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስለሌላቸው የሚያነቡትን ምንባብ በሰፊው እንደማይረዱትና በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ

ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው ይገልፃሉ፡፡ ከዚሁ ሀሳብ ጋር አያይዘው Weland (2017) እንደሚገልፁት ተማሪዎች አንድን ፅሁፍ በምን መልኩ አንብበው መረዳት እንዳለባቸው ባለማወቃቸው ሲቸገሩ ይስተዋላሉ፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለውም ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ላይ እንቀፋት ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች ስላሉ ነው (Graham, 1987)፡፡

ተማሪዎች አንብበው ለመረዳት እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ችግሮች ለመቅረፍም አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ብልሃቶችን መጠቀም እንዲችሉ ማበረታታት ተገቢ ነው (Graham, 1987)፡፡ እንደ Ells (1990) በበኩላቸው እንደሚገልፁት የመማር ብልሀቶች የሚባሉት ተማሪዎች መማራቸውን ቀላል፣ ፈጣን፣ አዝናኝና በራስ የሚመራ ውጤታማና ወደ አዲስ ሁኔታ የሚያሸጋግር ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት ናቸው፡፡ ከእነዚህም የመማር ብልሃቶች መካከል አንዱ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ነው (Rani፣ 2009)፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ማንበብን በመማር ሂደት ችግሮች ይስተዋሉባቸዋል፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚቆጠሩት ከተለያየ ባህለብዙ ማህበረሰቦችና የቋንቋ ተናጋሪዎች ስለሚመጡ ነው (Pang, 2008)፡፡ በዚህን ወቅት ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከመምህሮቻቸው እገዛን ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ካልሆነ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትን ስለማይጠቀሙ የሚነበቡ ምንባቦች በሚቀርቡላቸው ጊዜ አንብቦ ለመረዳት ከመምህራንና ጓደኞቻቸው ጋር ጥሩ የሚባል መስተጋብር ከሌላቸውና አዎንታዊ ግብረመልስ ካላገኙ በቋንቋው መማርና አንብቦ ለመረዳት ይቸገራሉ (Pang, 2008)፡፡

እንደ Oxford (1990) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች ማንበብን ሲማሩና አንብቦ ለመረዳት ጥረት ሲያደርጉ ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃትን ለምሳሌ፡- ጭንቀትን መቀነስ ከቻሉ አንብቦ ለመረዳት አይቸገሩም፡፡ ይህ ምሁር አያይዘው እንደሚገልፁት መምህራን ተማሪዎቻቸውን ማንበብ ለማስተማር ሲፈልጉ ከሚፈጠርባቸው ጭንቀት ወይም ፍርሃት እንዲላቀቁ ትምህርቱን ከመጀመራቸው አስቀድመው ለማዝናናት መሞከር፣ ሙዚቃ ማሰማትና ለማሳቅ መሞከር መቻል አንብቦ ለመረዳት ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃቶችን (መጠየቅንና በጋራ መስራትን) ተግባራዊ በማድረግ ራስ መር እንዲሆኑና ለሚፈጥሩት ስህተት ሃላፊነት እንዲወስዱ በማድረግ

አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ማሳደግ ይቻላል (Oxford,1990)። ተማሪዎች ማንበብን ሲማሩ የሚነበብ ምንባብ ሲቀርብላቸው ግልፅነት የጎደላቸው ሀሳቦች ሲያጋጥሟቸው እርስበርስ በመጠያየቅ፣ በታላሚው ቋንቋ ሲማሩ የሚከብዷቸውን በቋንቋው የተሻለ ከሚናገሩና ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር ትብብር በመፍጠር የማንበብ ሂደታቸውን ውጤታማ ማድረግ ይችላሉ።

እንደBaderawi (1992) እንደሚያስረዱት የቋንቋ ትምህርት በትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ የተገደበ አይደለም። ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በየትኛውም ቦታና ጊዜ ከጓደኞቻቸው ጋር ሲያነቡ፣ ሲጠይቁና እርስበርስ ግብረመልስ ሲሰጣጡ ይችላሉ። ይህ መሆኑ ደግሞ በቋንቋው አንብቦ መረዳት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ተማሪዎች ከመምህሮቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በሚፈጥሩት ጥሩ መስተጋብር በታላሚው ቋንቋ ያለምንም ጭንቀትና ፍርሃት እንዲያነቡ ሲደረጉ የደስታ ስሜት ስለሚፈጥርባቸው አንብቦ መረዳትን በቀላሉ ይለማመዱታል (Salam, 2013)። ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው ነው።

ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶን በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ተከናውነዋል። ለአብነትም ያህል፡- Choi(2011)፣ Doki & Katbelen (1991)፣ Rutman (1994)፣ Goodman (1994)፣ Simith (1985) እና Oxford & Borstok (1995) ተጠቃሽ ናቸው።

(Choi, 2011) በጥናቱ የውጪ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማሳደግ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትን ተግባራዊ አደረገ። በተከናወነው የቅድመና የድህረ ትምህርት ሙከራ ፈተናም የተገኘው ውጤት በአንብቦ የመረዳት ችሎታው ላይ ለውጥ አላሳየም። እንደ Doki &Katbelen (1991) ደግሞ ተማሪዎች ከመሰሎቻቸው ጋር ለመግባባት ከፍተኛ ልምምድ እንዲሁም ጥረት ካደረጉና ለመማር ጉጉትም ካደረባቸው በሂደት ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃታቸውን እያዳበሩ ስለሚሄዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ያድጋል። በሌላ በኩል Rutman (1994) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች የራሳቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ኖሯቸው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትን በአግባቡ ተግባራዊ አድርገው ማንበብን ከተማሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ይጎለብታል። በሌላ በኩል Oxford & Borstok(1995) እንደሚገልፁት የስሜት ህዋሳትን ያቀናጀ የትምህርት

አቀራረብ ስሜትን የመያዝና ቀልብን የመሳብ ሀይል ስላለው ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ አለው፡፡

አገር ውስጥ በቀጥታ ከማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ጋር የተያያዘ ጥናት በስፋት ባይገኝም የመማር ብልሃትና አንብቦ የመረዳት ችሎታን በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ አማረ (2001)፣ እንግዳ (1992)፣ እንድሪስ (2000)፣ሰላማዊት (2014)፣ ይሁኔ (2009) እና ወይንሸት (2007) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የአማረ (2001)፣ የእንግዳ (1992)፣ የእንድሪስ (2000)እና ይሁኔ (2009) ጥናቶች አንብቦ ለመረዳት በሚያስችሉ ዘዴዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡የይሁኔ (2009) በልዕለአዕምሮ አንብቦ የመረዳት ዘዴ ላይ የተመሰረተ ሲሆን የእንግዳ (1992) እና የአማረ (2001) ጥናት ግን በላዕላይ-ታህታይ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴልና በተራክቧዊ የማንበብ ማስተማሪያ ሞዴል ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው ይለያሉ፡፡

የእንድሪስ (2000) ጥናትና ይህ ጥናት የማንበብን ብልሃት የሚፈትሹ በመሆናቸው ከሌሎች ጥናቶች በተለየ የሚመሳሰሉ ቢሆኑም የእንድሪስ (2000) ጥናት ዋና ሀሳብን መለየት፣ መመስጠር፣ ማጠቃለልና ምስል ፈጠራ የተሰኙት የማንበብ ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያላቸውን ዝምድና የሚፈትሽ በመሆኑ ልዩነት አላቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱም ጥናቶች የማንበብ ብልሃቶቹ ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ የሚፈትሹ በመሆናቸው ይመሳሰላሉ፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚመሳሰሉት የወይንሸት (2007) እና የሰላማዊት (2014) ጥናቶች ናቸው፡፡ የወይንሸት (2007) ጥናት ትኩረት ያደረገው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና የፈተሸ ሲሆን በውጤቱም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማጎልበት ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዳለው አሳይቷል፡፡ ይህ ጥናት ደግሞ በማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ላይ ያተኩር እንጂ ብልሃቱ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ የሚፈትሽ በመሆኑ ከወይንሸት (2007) ጥናት ጋር ይለያያል፡፡ የሰላማዊት (2014) ጥናት ደግሞ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ የሚፈተሸ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ቢሆንም ከዚህ ጥናት ጋር በጊዜ፣ በቦታ ማለትም በትምህርት ቤትና በጥገኛ ተለውጦዎች የተለያየ ነው፡፡ የሰላማዊት

(2014) የጥናት ውጤት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፡፡

ይህ ጥናት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶን የፈተሸ በመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ከአብዛኛዎቹ ጥናቶች የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም በአገር ውስጥ ጥናቶች የታየው ክፍተት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት የመማር ብልሃቶች ያላቸውን ሚና በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች እንጂ በቋንቋ ትምህርት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት በራሱ ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ የፈተሹ አይደሉም፡፡

የተገኙ የጥናት ውጤቶችም አብዛኞቹ ከአገር ውጭ የተሰሩ ሲሆኑ በአገር ውስጥ የተካሄዱት ጥናቶች በማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ላይ በቀጥታ የተመሰረቱ አይደሉም፡፡በመሆኑም ይህ ጥናት ከላይ በተጠቀሱት ጥናቶች ውስጥ የተስተዋሉ ክፍተቶችን ለመሙላት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን እሉ ገላን ወረዳ አዳ ብሲል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በመመርመር አሳይቷል፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋን ለበርካታ ዓመታት ያህል አስተምሯል፡፡ በዚህም ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚያጋጥሟቸው ችግሮች አንደኛው አንብቦ የመረዳት ችሎታን የሚመለከት ስለመሆኑ ተገንዝቧል፡፡ ብዙ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ደካማ ስለመሆኑ በየጊዜው ከሚሰሯቸው የክፍል መልመጃዎችና መደበኛ ፈተናዎች ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን ጽሑፎች አንብበው የመረዳት ችግር ያለባቸው መሆናቸውን አጥኚው የታዘበ ሲሆን የመማሪያ መጽሐፉም አዘገጃጀት አንብቡና መልመጃዎቹን ስሩ የሚል አካሄድ የተከተለ ነው፡፡ በማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት በመታገዝ ማንበብን መማር ላይ የተከናወኑት የጥናት ውጤቶችም ብዙዎቹ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው ሲገልፁ ጥቂቶቹ ደግሞ፣ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ዝምድና እንደሌለው አሳይተዋል፡፡ ይህ መሆኑም ለዚህ ጥናት መካሄድ እንደ ሌላ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል፡፡

ስለዚህ ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር የተያያዙ ችግሮች ዋና ምክንያታቸው ከማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ጋር የተያያዙ ይሆን? የሚል ጥያቄ ለማንሳት አጥኚውን ግፊት ሰጥተውታል። ስለዚህ የጥናቱ ዓብይ ትኩረት በማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት በመታገዝ የሚደረግ የማንበብ ትምህርት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ የፈተሸ ሲሆን በዚህም መሰረት ጥናቱ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል።

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፡-

1. ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ አለውን?
2. ማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የመተንበይ ድርሻቸው ምን ያህል ነው? የሚሉ ናቸው።

## 1.3 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታና ከማንበብ ተነሳሽነት ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው።

### 1.3.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

1. ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ እንዳለውና እንደሌለው መፈተሽ፤
2. ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ የመተንበይ ድርሻ እንዳለውና እንደሌለው መፈተሽ፤

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ለቋንቋ መምህራን፣ ለተማሪዎች፣ ለተመራማሪዎችና ለቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች በማስገኘት ረገድ አስፈላጊ ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

1. ለመምህራን የተማሪዎቻቸውን ማህብረ-ስሜታዊ ብልሃት አተገባበር በመለየት የትምህርት አቀራረባቸውን፣የማስተማሪያ መሳሪያዎቻቸውን፣ የዕለት

ዕቅዶቻቸውን ከማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ትግበራ አንፃር እንዲያዘጋጁ ሊረዳ ይችላል፡፡

2. ተማሪዎች የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ተግባራትን ተግባራዊ በማድረግ ማንበብን በመማር ረገድ ሊያግዝ ይችላል፡፡

3. በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኝዎች እንደመነሻ በመሆን ሊጠቅም ይችላል፡፡

4. ለቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ማንበብን ማስተማሪያ የሚሆኑ ምንባቦችንና ተግባራትን በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሲያካትቱ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትን እንድያካትቱ ጥቆማ ይሰጣል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን እሉ ገላን ወረዳ ኦዳ ብሲል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በአስረኛ ክፍል ከሚማሩ አምስት ምድብ ተማሪዎች አስረኛ (D) የመማሪያ ክፍልን ከዕድል ሰጪ ንሞና ውስጥ ቀላል የዕጣ ንሞና ዘዴን ተጠቅሞ በመምረጥ ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ፈትሿል፡፡ በጥናቱ የተፈተሹት ተላውጦዎችም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ናቸው፡፡ በመሆኑም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት በነፃ ተላውጦ ስር፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ደግሞ በጥገኛ ተላውጦ ተካተው ታይተዋል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት የተማሪዎችን ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትንና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተዛምዶን የሚፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ትኩረት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን እሉ ገላን ወረዳ ውስጥ ከሚገኙት ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል አንዱ ላይ ብቻ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ በጥናቱ ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ እንዲሁም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማወቅና በመረጃነት ለማዋል ጥቅም ላይ የሚውሉት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናዎች ተማሪዎች ብዙ ጊዜ የለመዷቸው እንጂ ሁሉንም የፈተና ዘዴዎች ማካተት የሚችሉ ሊሆኑ ስለማይችሉ

የተማሪዎችን ውጤት በተወሰነ ደረጃ ውስንነት እንዲኖረው ሊያደርግ እንደሚችል ይገመታል፡፡

## 1.7 የቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦች ብያኔ

### *1.7.1.* ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት

ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ በክፍል ውስጥም ሆነ በውጪ የሚገጥሟቸውን የስሜትና የመነቃቃት ችግሮች ከጓደኞቻቸውና ከታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ተራክቦ በመፍጠር በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ብልሃት ነው፡፡

### 1.7.2. አንብቦ የመረዳት ችሎታ

የአንድን ፅሁፍ ጥቅል መልዕክት አንብቦ መረዳትን፣ከፅሁፉ ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ መረጃዎችን መለየትንና አንድምታዊ ሃሳቦችን የመገንዘብ ችሎታን ይመለከታል፡፡

### 1.7.3. የማንበብ ተነሳሽነት ብልሃት

የተለያዩ የማንበብ ክንውኖችን በተከታታይ ሳይታክቱ በዘላቂነት ለመተግበር የሚያስችል ባህርይ መላበስ መቻል ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

### 2.1 የቋንቋ መማር ብልሀቶች ምንነት

Kohen (1998)ን ዋቢ በማድርግDornyei (2005) እንደሚያስረዱት የመማር ብልሃት በተማሪዎችና በመምህራን ሆን ተብሎ እና በንቃት የሚመረጥ የመማር ሂደት ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ ያልተሰጠው እና አወዛጋቢ ሀሳብ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ Griffiths (2004) እንደሚገልፁት በቋንቋ መማር ብልሃት ዙሪያ በርካታ አጥኚዎች O.Mally and Chamot(1990) እና Rubin (1978) ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡

የመማር ብልሀት ማለት ተማሪዎች አንድን የመማር አላማ ለመከታተል ወይም የመማር ተግባርን በእጅ ለማከናወን የሚያስችል ዘዴ መሆኑን Salovoara (2005) ያስረዳሉ፡፡ ተማሪዎች ትርጉም ባለው መንገድ ብልሃቶችን ለመጠቀም መቼ እና እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅንም ይጠይቃል፡፡ ተማሪዎች በብልሃት አጠቃቀማቸው አንዱ ከሌላው ይለያያሉ፡፡ ይህም በመሆኑ ተማሪዎች ብልሃቶችን እንደየምርጫቸው ሊጠቀሙ ይችላሉ ወይም በንቃት ሆን ብለው በምን ያህል ደረጃ መጠቀም እንዳለባቸው ይወስናሉ በማለት Salovoara(2005) ያስገነዝባሉ፡፡

O.Mally and Chamot(1990)ን Dornyei (2005) ዋቢ አድርገው እንደሚያስረዱት የቋንቋ መማር ብልሃቶች ማለት ልዩ ልዩ ትምህርቶችን ወይም ባህርያትን እያንዳንዱ ግለሰብ በራሱ ለመረዳት፣ ለመማር ወይም የተገኘ አዲስ መረጃን ይዞ ለመቆየት የሚያገለግሉ ብልሃቶች ናቸው፡፡ እንደDornyei (2005) አገላለጽ የቋንቋ መማር ብልሃት ማለት ለመማር የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ለመለየት የሚያስችል መንገድ ሆኖ ለመማር ቀላል የሆነና ጠቃሚውን ከማይጠቅመው የሚለይበት፣ የማስታወስና የድግግሞሽ ተግባራትን የሚያካትት ነው፡፡

እንደ Williams and Burden(1997) ገለፃ ደግሞ አዕምሯዊ የመማር ብልሃቶች ተማሪዎች ትምህርታቸውን በራሳቸው ትርጉማዊ ለማድረግ የሚገለግሉባቸው መንገዶች እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ Oxford (1999)ን Dornyei (2005) በመጥቀስ እንደሚገልፁት ተማሪዎች በራሳቸው የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ማለትም ዝርዝር ድርጊቶችን፣ ባህርያትን፣ ሂደቶችን ወይም ቴክኒኮችን በመጠቀም የሁለተኛ ቋንቋ ችሎታቸውን

ለማዳበር የሚጠቀሙባቸው ሆነው አዲሱን ቋንቋ ለመጠቀም ወይም ለመረዳት ነገሮችን የሚያመቻቹባቸው መንገዶች ናቸው፡፡

የመማር ብልሃቶች አንድን መረጃ በሂደት ተቀብለን ካከማቸን በኋላ መረጃው ተመልሶ ለተፈለገው አካል የሚስጥበት ሂደት ነው (Winter፣ 2004)፡፡ የቋንቋ ለመዳን ለማከናወን በሰዎች መካከል የብልሃት አጠቃቀም ልዩነት በመኖሩ አንዳንድ ተማሪዎች ብልሃቶችን የመጠቀም ችሎታ ሲኖራቸው አንዳንዶች ደግሞ የላቸውም፡፡ Rubin (1975) እና Stern (1975)ን ዋቢ አድርገው Dornyei (2005) እንደሚያስረዱት ደግሞ የመማር ብልሃት አንድን ሃሳብ ለመረዳት፣ እንደገና ለማዋቀር፣ ትርጉም ያለው አረፍተ ነገር ለመመስረት የሚያውቁትን በሰፊውና በአዲስ መልክ የቋንቋ ሂደቶችን ለመጠቀም፣ አዕምሯዊ ምስል በመፍጠር ነገሩን ለመረዳት፣ ስለሚማሩት ቋንቋ ጊዜያዊ የሆነ አዕምሯዊ ምስል ለመፍጠር የሚያስችሉ ናቸው፡፡

እንደ Rosenshine and Meister (1992) ገለፃ ማንኛውም ብልሃት ቀጥተኛ የሆነ ሂደትን የሚከተል አይደለም፡፡ ይልቁንስ ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ ነገሮችን እንዲያከናውኑ የሚያመቻች ሆኖ ያለፈ ልምድን በመጠቀም ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ ነው፡፡ Andorson (1991)ን ዋቢ በማድረግ Rosenshine and Meister (1992) እንደሚሉት አዕምሯዊ ብልሃቶች በማንበብ ጊዜ በጥቅል ለማሰብ፣ አስቸጋሪ ፅንሰ ሀሳቦችን ለመለየትና ጠቃሚ መረጃዎችን ለማጠቃለል ያስፈልጋሉ፡፡

የመማር ብልሃቶች አዕምሯዊ ተግባራት በመሆናቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አዳዲስ ይዘት ወይም በጣም አስቸጋሪ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ሲጠየቁ የተለየ ጉልበት ሳይጠቀሙ በፍጥነትና በቀላሉ ለማከናወን የሚያስችሏቸውን መንገዶችን ለማግኘት የራሳቸውን ጥረት ያደርጋሉ (Mark፣ 2008)፡፡ ከዚህም መረዳት የምንችለው ተማሪዎች ብልሃቶችን በመጠቀም ተግባራትን የሚያከናውኑባቸው መንገዶች ናቸው፡፡

እንደ O.Mally and Chamot(1990) እንደሚያስረዱት በአሜሪካ ከፍተኛ ተደማጭነት ያለው ወይም ተፅዕኖ አሳዳሪ ከሚባሉት ጎራ የሚጠቀሱት የብልሃት ባለሙያ ክላዮርን እንደሚሉት የመማር ብልሃቶች ተግባራትን በንቃትና በራስ ተሳትፎ የሚመራ ለማድረግ የሚረዱ መሳሪያዎች፣ የማንኛውም ትምህርት መለያ ባህርያትን፣ እምነትን ወይም ስሜትን ለቋንቋ ለመዳ ወይም ቋንቋን ለመረዳት አልያም ደግሞ የነበረን ዕውቀት ወደ አዲስ ዕውቀት ለማሸጋገር ራሳቸውን የሚያግዙባቸው መንገዶች ናቸው፡፡

የመማር ብልሃቶች ትኩረት ተማሪዎች በተማሪ ተኮር ትምህርት ጊዜ አስፈላጊ ነጥቦችን በራሳቸው በመምረጥ መጠቀም እንዲችሉና ጠቃሚ ወደ ሆነ የማንበብ ሂደት እንዲመጡ ማገዝ፣ችግራቸውን ለመፍታት መረጃ በመሰብሰብ ሂደት ላይ የሚያተኩር ነው (Blok፣ 1993)፡፡ በሌላ በኩል Oxford(1990) እንደሚገልፁት አዕምሯዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ተግባራትን፣ ባህርያትን፣ ደረጃዎችን ወይም ደግሞ ቴክኒኮችን አንድን ምንባብ በማንበብ ሂደት ላይ ተግባራዊ በማድረግ የመፍታት ችሎታቸውን ለማሻሻል የሚጠቀሙባቸው ናቸው፡፡

እነዚህ ብልሃቶች መረጃ ማከማቸትን፣ ፈልጎ ማግኘትን፣ ነገሮችን ማስተካከል ወይም አዲስ ቋንቋን ለመጠቀም ሊያመቻቹ ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ ተማሪዎች የመማር ብልሃቶች ቀላልም ሆነ ከባድ ተግባራት ተማሪዎች ሲገጥሟቸው እንደመማር ብልሃት ምርጫቸው የሚያከናውኑባቸው ብልሃቶች ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች የአንድን ትምህርት ዓላማ ግብ የሚያደርሱበት መንገድ ነው፡፡ ይህን ለማከናወን ብልሃቶችን መቼ፣ የት እና እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ማወቅ ተገቢ ነው (Brown፣ 1994)፡፡

Hurd and Lewis(2008) እንደሚያስረዱት በአጠቃላይ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ጊዜ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ለማስወገድ ሆን ብለው በመምረጥ የሚጠቀሙባቸው ድርጊቶች ወይም ሂደቶች ናቸው፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚጠቀሰው የቋንቋ ተማሪዎች ትምርታቸውን እንዴት ይቆጣጠራሉ? የቋንቋ ብቃታቸውን ለማሻሻል ብልሃቶችን እንዴት ይጠቀማሉ? የሚሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ምክንያቱም በተማሪዎች መካከል ግለሰባዊ ልዩነቶች አሉ፡፡

## 2.2 የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ምንነት

ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ማህበራዊ እና ስሜታዊ የመማር ብልሃት ተብሎ ይከፈላል (Oxford፣1990) እና (Stern፣ 1983)፡፡ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች ቋንቋን በሚማሩበት ወቅት ከጓደኞቻቸው ጋር ነፃ ሆነው በራሳቸው መንገድ ታላሚውን ቋንቋ የሚማሩበት ብልሃት ነው (O.Mally and Chamot1990)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Oxford(1990) እንደሚያስረዱት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት በተማሪዎች ተግባራዊ ሲደረግ በታላሚው ቋንቋ የተለያዩ ተግባራትን ከጓደኞቻቸውና ከመምህሮቻቸው ጋር እየተጠያየቁ፣ እየተረዳዱና ጥሩ የሚባል መስተጋብር እየፈጠሩ ለመማር ወይም ለማንበብ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች ስሜት፣ ተነሳሽነት፣ ዝንባሌና ፍላጎት ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ ቋንቋን ሲማሩ የሚፈጠሩባቸውን የጭንቀት፣ የፍርሃት በአጠቃላይ መጥፎ ስሜትን ለመቆጣጠር የሚችሉበት ብልሃት ነው፡፡ ምክንያቱም መጥፎ ስሜት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ትምህርታቸውን ሲማሩ ውጤታማ እንዳይሆኑ ሲያደርግ ጥሩ የሆነ ስሜት ሲፈጠርባቸው ደግሞ የመማር ፍላጎታቸውን በማነሳሳት ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል (Oxford፣ 1990)፡፡ በሌላ በኩል Stern (1983) እንደሚያስረዱት ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሲማሩ የሚፈጠሩባቸውን የመነሳሳትና የመነቃቃት ችግሮችን በብቃት ለመቋቋም ያስችላቸዋል፡፡

ተማሪዎች ትምህርታቸውን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ በሚማሩበት ጊዜ በሚኖራቸው መስተጋብር ለታላሚው ቋንቋና ለቋንቋው ተናጋሪዎች ባህል፣ እሴትና ልማድ እንግዳ ሊሆኑ ስለሚችሉ በቋንቋ ለመማር ወይም ለማንበብ ፍላጎትና መነቃቃት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን የመረበሽ ስሜት ስለሚፈጠርባቸው ራሳቸውን እንደ አንድ የቋንቋው ተማሪ በመቁጠር በታላሚው ቋንቋ ለመማር መነሳሳት፣ የቋንቋውን ተናጋሪዎች ባህል፣ እሴትና አመለካከት ለመጋራት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በታላሚው ቋንቋ መማር ብሎም ማንበብ ያስደስታቸዋል (Stern፣ 1983)፡፡

ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከመማር ብልሃቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን ተማሪዎች እርስበርሳቸው እንዲተጋገዙ፣ መተጋገዛቸውንም የምንፈትሽባቸውና በተጨማሪም መረበሽን ለመቋቋም የሚጠቅም ብልሃት ነው (Dornyei፣ 2005)፡፡ እንደ Gaber (2006) በበኩላቸው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት በተማሪዎችና በመምህራን መካከል መደበኛ ባልሆነው የመማር ማስተማር ሂደት መልካም የሚባል መስተጋብር በመፍጠር በቋንቋ መማራቸውን እንዲወዱት የሚያደርግ ብልሃት ነው፡፡ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ምን አይነት ስሜት እንደሚሰማቸው እያሰቡ ከጓደኞቻቸው ጋር እየተባበሩ እንዲማሩ ያደርጋቸዋል:: ብልሃቱ ተማሪዎች እርስበርስ በመተጋገዝና ያልተረዱትን ከጓደኞቻቸው፣ ከመምህራንና ከማህበረሰቡ በመጠየቅ መማራቸውን የሚያሳልጡበት ነው (Oxford፣1990)፡፡ እንደ Rubin (1987) ገለፃ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሲማሩና ሲያነቡ የሚፈጠርባቸውን አሉታዊ የሆኑ ስሜቶችን ለምሳሌ ተነሳሽነት ማጣትን፣ ጭንቀትንና ውጫዊና ውስጣዊ ተፅዕኖዎችን ለመቆጣጠር ያስችላል፡፡

## 2.3 የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ክፍሎች

ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት የተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች እንዳሉት (Oxford፣ 1990) እና (Rubin፣ 1987) ይገልፃሉ፡፡ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ያላቸውን እንግዳ ስሜት በመጠያየቅ፣ በመረዳዳት፣ ስሜትን በመቆጣጠር እንዲሁም የሌሎችን ማንነት እንደ ራሳቸው በመውደድ የሚተገብሩት ብልሃት ነው (Rubin፣ 1987)፡፡ በመሆኑም የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ንዑሳን ክፍሎች ጭንቀትን መቀነስ፣ ራስን ማበረታታት፣ ጥያቄ መጠየቅና በትብብር መስራት እንደሆኑ (Oxford፣ 1990) ይገልፃሉ፡፡

### 2.3.1 ጭንቀትን መቀነስ

ሰዎች እጅጉን የተጋነነ ጭንቀት የሚታይባቸው ከሆነ የሚሰጣቸውን ተግባር በብቃት ለመወጣት ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ስራቸውን በሚገባ አከናውነው ማግኘት ያለባቸውን ነገር ማግኘት እንዳይችሉ ያደርጋል፡፡ ይህ ንኡስ ብልሃት የተማሪው የጭንቀት መጠን ሲጨምር የማጣራት ስራም በተመሳሳይ መንገድ ስለሚጨምር በዚህ ጊዜ የቋንቋ ተማሪው ከውጭ ወደ ውስጥ ማግኘት ይችል የነበረውን እውቀት ስለሚታገድ የሚያገኘው ግብዓት ወይም የመማር አቅሙ ይቀንሳል፡፡ ነገር ግን ተማሪው ብዙ የማይጨነቅና በተዝናኖት የሚማር ከሆነ የማጣራቱ ተግባር ስለሚቀንስ ግብዓቱ ይጨምራል፡፡ ስለዚህ የተማሪው ጭንቀት ውስጥ መግባት ቋንቋ በመማሩ ሂደት (ተግባር) ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስላለው ሊፈጠሩ የሚችሉ ጭንቀቶችን መቀነስ ተገቢ ነው (Ells፣1990)፡፡

ጭንቀትን መቀነስ ሲባል ተማሪዎች በቋንቋው ሲማሩ የሚገጥሟቸውን ችግሮች በጥልቀት በማሰብ፣ አዎንታዊ የሆኑ ሃሳቦችን በማሰብ፣ከውስጥ በረጅሙ በመተንፈስና ከራስ ጋር በመነጋገር ማስተካከል ያስፈልጋል (Magno፣2010)፡፡ በሌላ በኩል Oxford (1994) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች የማህበረ-ስሜታዊ፣ አዕምሯዊና ልዕለ-አዕምሯዊ የመማር ብልሃትን አጣምረው የሚጠቀሙ ከሆነ ታላሚውን ቋንቋ በሚማሩበት ወቅት የሚፈጠርባቸው ጭንቀት አነስተኛ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች ቋንቋውን ሲማሩ የሚፈጠሩባቸውን አሉታዊ ስሜቶች ለመቆጣጠር ከጓደኞቻቸው፣ ከመምህራንና ከታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር መስተጋብር በመፍጠር ጭንቀትን በመቀነስ የመማር ወይም የማንበብ ሂደትን ማፋጠን ይቻላል (Oxford፣ 1990)፡፡

### 2.3.2 ጥያቄ መጠየቅ

ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የሚቀርብላቸውን ተግባር ሲያከናውኑ ግልፅነት የሚጎድላቸውን ተግባራት ጥያቄ በመጠየቅ ማብራሪያ የሚያገኙበት ብልሃት ነው (Guthrie and Wigfield፣ 2000)። ጥያቄ መጠየቅ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማሳደግ የሚረዳ ብልሃት ሲሆን ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ ባለቤቶች ጋር ሀሳብ በመለዋወጥ፣ ባህልን በመጠየቅ ለመረዳት በመሞከር፣ የማህበረሰቡ እሴቶችን በመጠየቅ መረዳት መቻል በቋንቋው ለመማር ያስችላቸዋል። በመሆኑም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ማንበብን ሲማሩ ቡድን በመስራት ሊሆን ይችላል ስለአዳዲስ ቃላት ፍቺ ጥያቄ በመጠየቅ፣ ስለዐረፍተ ነገሮች አደረጃጀትና ይዘታቸው ማብራሪያ በመጠየቅና ስለሚሰጣቸው ምላሽ በንቃት መቀበልና መሳተፍ ይኖርባቸዋል (Magno፣ 2010)።

### 2.3.3 በትብብር መስራት

የመማር ማስተማር ሂደቱ በትብብር የመማር ተግባራት የተሞሉበት ከሆነ ማንበብን በመማር ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ቃላትን ለመረዳት፣ ለተለያዩ ሀሳቦችና አገላለፆች ፍቺ ለመስጠትና ለመረዳት እርስበርሳቸው ይተጋገዛሉ። ከዚህም ባሻገር ተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀታቸውን በመጠቀም በፅሁፉ ውስጥ የሚተላለፈውን ሃሳብ ለመረዳት ከፍተኛ የሆነ ጥረት ያደርጋሉ። በዚህ ወቅት በምንባቡ ውስጥ ስለተነሳው ሀሳብ ግልፅ የሆነላቸው ተማሪዎች ግልፅ ላልሆነላቸው ሌሎች ተማሪዎች ፅንሰሃሳቡን ያብራሩላቸዋል። እንደ Stevens (1991) አገላለፅ በትብብር የመማር ብልሃት የሚተሳሰሩት ቡድኖች አባላት የተለያየ ክህሎት ያላቸው በመሆኑ አንደኛው ተማሪ ከሌላኛው ተማሪ ጋር በሚያደርገው ንግግር ወይም ውይይት እንዲሁም አንደኛው ተማሪ ሌላኛውን ለማገዝ በሚያደርገው ጥረት የተለያዩ የንባብ ስልቶችን እንዲያውቁ ስለሚያደርጋቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማጎለበት ይረዳቸዋል።

አለማየሁ (2009) Jalilifer(2010)ን ጠቅሰው እንደሚገልፁት አንዳንድ ሰው ነገሮችን በቀላሉና ቶሎ ሊያስታውስ ይችላል፤ ሌላው ደግሞ ነገሮችን በቀላሉ የማስታወስ ችሎታው ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ከአቻ ጋር በመሆን የሚከናወን የመማርና የማንበብ ሂደት በማስታወስ ችግር ምክንያት የሚከሰትን የመረጃ ክፍተት ለመሙላትና ለማስተካከል ያስችላል። በመሆኑም ትብብራዊ የመማር ብልሃት ተማሪዎች ነገሮችን ረዘም ላለ ጊዜ ያህል እንዲያስታውሱ በማድረግና የማስታወስ ችሎታቸውን በማነቃቃት

በኩል ትልቅ ደርሻ አለው። ስለዚህ ተማሪዎች በሚመሰርቱት ቡድን ማዕቀፍ ውስጥ ሆነው ማንበብን ሲማሩ አንዱ የሚያውቀውን ሌላው ሳያውቀው ስለሚችል እየተረዳዱ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ተግባራዊ ሲያደርጉ በመካከላቸው ትልቅ የግንኙነት መረብ ይፈጥራሉ።

## 2.5 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምንነት

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለአንድ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ የሚዘጋጅን ምንባብ በክፍል ደረጃው ተመድበው የሚገኙ ተማሪዎች ያለ ምንም ችግር አንብቦ ሃሳቡን መረዳት መቻልን ይመለከታል። ከዚህም በተጨማሪ አንድን ፅሁፍ አንብቦ ፍቺውን ለማግኘት የሚከናውን ንቁ ሂደት ሲሆን ከፅሁፉ ጋር በንቃት የመነጋገር እና ከሚነበበው ፅሁፍ ፍቺ የማመንጨት ችሎታ ነው።

አንብቦ ለመረዳት ችሎታ አስተዋፅኦ ከሚያደርጉ ምክንያቶች ውስጥ የፅሁፍ መዋቅር አይነት፣ የማስተማሪያ ብልሃቶች፣ የምንባቡ ውስብስብነት፣ ተማሪዎች አንብቦ ለመረዳት የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶች፣ የቀደመ እውቀት እና መነቃቃት ተጠቃሾች ናቸው። እንዲሁም አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተግባር የህብረተሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ አውድ፣ ትምህርት ቤትን፣ ማህበረሰብን፣ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ (የገቢ ምንጭ እና የክፍል ጓደኞች፣ ዘር፣ ጎረቤት፣ የትምህርት ቤት ባህል)፣ የቋንቋ አጠቃቀም ሂደትን፣ ተማሪዎች ስለራሳቸው ያላቸውን አመለካከትን ሁሉ መሰረት ያደርጋል (Smith፣ 1980)።

አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተለዋዋጭነት ያለው በሂደት የመገንዘብ እና እውቀትን የመገንባት ተግባር ነው። የቀረበውን ምንባብ አዕምሯዊ እና ሁኔታዊ ብልሃቶችን እንዲሁም ላይ-ታች እና ታች-ላይ የማንበብ ሞዴልን ተግባራዊ በማድረግ የፅሁፉን መልዕክት መረዳት መቻል ነው (Johnson፣1978)። ከዚህም መረዳት የሚቻለው አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአዕምሯዊ ብልሃቶች እና በሁኔታዊ ሞዴሎች ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ነው።

አዕምሯዊ ብልሃቶች ሲባልም የሚነበበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ሊተላለፍ የተፈለገውን ሃሳብ ከአዕምሮ ጋር በማዛመድ በምንባቡ ውስጥ ለሚገኙ አዳዲስ ቃላት እና ሀረጋት በአዕምሮ ውስጥ ተጨባጭ የሆነ ውክልና እየሰጡ የሚተገበር የአንብቦ መረዳት ችሎታ ብልሃት ነው። በዚህ ጊዜ አንባቢው የዐረፍተ ነገሮችን ሃሳብ በማስተሳሰር አዕምሯዊ በሆነ መንገድ የምንባቡን ውስብስብ ትልም፣ ታሪክ እና ጭብጥ መረዳት

መቻል አለባቸው፡፡ በሌላ በኩል አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሁኔታዊ ሞዴልን መሰረት ያደረገ ነው ሲባል በምንባቡ የሚነሳውን ሀሳብ ከራስ የቀደመ ዕውቀት ጋር በማስተሳሰር ለመረዳት መሞከር ነው (Johnson፣ 1978)፡፡

ተማሪዎች ለሚያነቡት ነገር አዕምሯዊ ውክልና እየሰጡ የሚያነቡ ከሆነ ችግርን ለመፍታት በሚያስችል ደረጃ በማሰብ፣ መረጃ በማጣቀስ እና በመመዝገብ ትርጉም ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ውጤታማ አንባቢያን ግብ ይጥላሉ፤ የሚሰጡትን ፍቺ ይቆጣጠራሉ፤ እንዲሁም የተረዱትን ነገር ለመግለፅ ይሞክራሉ (Johnson፣ 1978)፡፡ አንብቦ የመረዳት ችሎታ በራስ ተመርቶ ግብ በመጣል እና በፍላጎት ላይ በመመስረት አንባቢው በማንበብ ሂደት የሚያጋጥሙትን ችግሮች የሚቀርፍበት፣ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን አላስፈላጊ ከሆኑት በመለየት የአንድን ነገር ባህርይ በትክክል ለመረዳት ግብን መሰረት አድርጎ የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት በራስ የሚመራ ማንበብ ተነሽነትን ከማስገኘቱም በተጨማሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበትም የጎላ ድርሻ አለው (Moorman and wood፣ 1990)፡፡

## 2.4 ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ

አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤታማነት በተለያየ መንገድ እገዛ እንደሚያደርጉ ይታመናል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ተማሪዎች ብልሃቶቹን በእኩል ደረጃ ይጠቀማሉ ብሎ በእርግጠኝነት መናገር አይቻልም (Richards፣ 1985)፡፡ ምክንያቱም የብልሃቶቹ አጠቃቀም፣ ተማሪዎች ስለብልሃቶቹ ያላቸው እውቀት፣ ባህላዊ ዳራ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ስለሚወሰን ነው፡፡

እንደ Grebe and Stoller(2002) ገለፃ ቀደም ባለው ዘመን ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር የጎላ ተዛምዶ አልነበረውም፡፡ ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደረጉ ጥናቶች ውጤት እንደሚታየው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል እንደ Boakye (2012) ገለፃ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው ከተሰጣቸው ምንባብ ውስጥ የሚተላለፈውን መልዕክት በአግባቡ እንዲረዱ አስችሏቸዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

### 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ መጠናዊ በመሆኑ ተዛምዷዊ የምርምር ዘዴን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የተማሪዎች የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት አጠቃቀም በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበ ሲሆን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ደግሞ በአንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ተሰብስቧል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ የዋለው መረጃም በጽሑፍ መጠይቅና በፈተና ከተሰበሰበ በኋላ መጠናዊ በሆነ የጥናት ስልት ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን በእሉ ገላን ወረዳ ከሚገኙ ሶስት ትምህርት ቤቶች መካከል በኦዳ ብሲል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያትም አጥኚው መደበኛ ስራውን የሚሰራበት በመሆኑ መረጃ ለማግኘት ያለውን አመቺነት ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቱ በስነ ንሞና ዘዴ ተመረጠ፡፡ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችም የተመረጡት የንሞና ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ከተመረጡት የጥናቱ ተሳታፊዎች የሚገኝ መረጃ በቂ ምላሽ ያስገኛል በሚል ታስቦ ነው፡፡ በኦዳ ብሲል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም 400 የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአምስት ምድብ ተመድበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ሲሆን በእያንዳንዱ የመማሪያ ክፍል 80 ተማሪዎች ተመድበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በተራ የእጣ ናሙና ዘዴ መሰረት ከአምስት ምድቦች የአስረኛ “D” ክፍል ተማሪዎችን በመምረጥ በድምሩ 80 ተማሪዎች ተወስደው የጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ 80 ያህል ተማሪዎች ማለትም 20% የሚሆኑት በጥናቱ እንዲሳተፉ የተደረገበት ምክንያትም ከተጠኚዎች የሚሰበሰበው መረጃ ሲተነተን የሚገኘው መረጃ አስተማማኝ እንዲሆን በመታሰቡ ነው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ይህ ጥናት ሲካሄድ ተግባራዊ የተደረጉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናና ለማንበብ ተነሳሽነት ብልሃትን የሚለካ የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው።

### 3.3.1 አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና

ይህ ጥናት ይዟቸው የተነሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችለው የመጀመሪያው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ያገለገለው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ነው። የአንብቦ መረዳት ፈተናውም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ጥቅም ላይ ውሏል። በመሆኑም የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገባ ከሁለት ምንባቦች በአጥኚው አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና የተዘጋጀ ሲሆን ከመጀመሪያው ምንባብ አስር የምርጫ ጥያቄዎች፣ ከሁለተኛው ምንባብ ደግሞ ተጨማሪ አስር ምርጫ ሰጪ በድምሩ ሃያ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። የተዘጋጁት ምንባቦች መረጃ ሰጪ፣ ከራሳቸው የክፍል ደረጃ ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ እንዲሆኑ ተደርጓል። አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመፈተሽ የተዘጋጁት ጥያቄዎች በአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በጥናቱ አማካሪ ተፈትሸው የሚስተካከሉት ተስተካክለው ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲውሉ ተደርጓል። ከዚህም ባሻገር አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናው በሌሎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ባልሆኑ 40 ተማሪዎች ላይ ተሞክሮ በክሮምባኽ አልፋ ቀመር ተፈትሾ .742 ሆኖ ስለተገኘና አስተማማኝ ስለሆነ የዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ አገልግሏል።

### 3.3.2 የጽሑፍ መጠይቅ

ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ተግባራዊ የተደረገበት ዋናው አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃትን ለመለካት ነው። በመሆኑም ማስተዋል (2011) በቀጥታ ከዊግፌልድና ጎትሪ (1997) ወስደው ጥቅም ላይ ያዋሏቸውን መጠይቆች ለዚህ ጥናት የሚመቹትን በመምረጥ 22ቱን ጥቅም ላይ አውሏል። መጠይቁም የማንበብ ግለብቃት እምነትን፣ ውስጣዊና ውጫዊ የማንበብ ተነሳሽነትን፣ ማህበራዊ የማንበብ ተነሳሽነትን አማክሎ እንዲይዝ ተደርጓል። ከዚያም የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ ለዋናው ጥናት ተሳታፊ ተማሪዎች ከመጠየቃቸው በፊት በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በአጥኚው አማካሪ ተገቢነታቸው በትክክል ተገምግሞ እንደገና ተሻሽሎ ከተዘጋጀ በኋላ ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲውል

ተደርጓል፡፡ ከዚህም ባለፈ የጽሑፍ መጠይቁ አስተማማኝነት በሌሎች 40 ተማሪዎች ላይ ተሞክሮ በክሮምባኽ አልፋ ቀመር ሲፈተሽ .768 ሆኖ በመገነቱ ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ውሏል፡፡

በዚህ መልክ በሚገባ ተደራጅቶ የተዘጋጀው መጠይቅ ትኩረትም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትን ተጥቅሞ ማንበብን መማር የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት እንደሚያሻሽል ወይም እንደማያሻሽል ለመፈተሽ ነው፡፡ መጠይቆቹ በዓይነታቸው ዝግ ሆነው በሬቲንግ ስኬል መሰረት የተዘጋጁ ሲሆን እያንዳንዳቸውም አራት አማራጮችን የያዙ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ጥያቄ ፊት ለፊት ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ የያዙት ዋጋ 4 = በጣም እስማማለሁ 3= እስማማለሁ 2 = አልስማማም 1 = በፍጹም አልስማማም በሚሉ አማራጮች በሰንጠረዥ እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

## 3.4 የአጠናን ሂደት

ይህንን ጥናት ለማካሄድ በመጀመሪያ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተዘጋጁ ሲሆን የተዘጋጁት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችም በመምህራንና በጥናቱ አማካሪ ተገምግመው ተገቢነታቸው ከታየ በኋላ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ በመሆን እንዲያገለግሉ ተደርጓል፡፡

ዋናውን ጥናት ለማካሄድ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ከተዘጋጁ በኋላ የኦዳ ብሲል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር፣ መምህራንና ሌሎች የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ባሉበት ተማሪዎች በጥናቱ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ለመሆናቸው ይሁንታቸውን ከገለፁ በኋላ ከአምስት  የአስረኛ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ አንዱ በዕድል ሰጪ የንሞና ዘዴ አማካይነት በእጣ እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም በዕጣ የተመረጠው ምድብ ተማሪዎች በተመሳሳይ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያነት የሚውለውን ፈተና ተፈትነዋል፤ የማንበብ ተነሳሽነትን ለመለካት የዋለውን የጽሁፍ መጠይቅም ሞልተዋል፡፡

የጥናቱ ሂደት የተስተካከለ እንዲሆን የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተሰጡ ማጠቃለያዎች በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ወቅት በሚፈጠሩ ስህተቶች ምክንያት እንዳይዛቡ ለማድረግ ጥንቃቄዎች ተደርገዋል፡፡ ከተደረጉ ጥንቃቄዎች መካከልም መረጃዎቹ የተሰበሰቡባቸው ቀናት ምቹ መሆናቸውን በማረጋገጥ ተመርጠዋል፡፡ በተመረጡት ምቹ ቀናትም የጥናቱን አላማ በተመለከተ ተጨማሪ ዝርዝር ማብራሪያ ለጥናቱ ተሳታፊ

ተማሪዎች ተሰጥቷል፡፡ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተናው ወቅትም ይሄው ጥንቃቄ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም መረጃዎችን በመሰብሰብ ሂደት በሚፈጠሩ ችግሮች ምክንያት የመረጃ መዛባት እንዳይከሰትና በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎች እንዳይፈጠሩ ከፍተኛ ትኩረት ተደርጓል፡፡ ከዚያም ከማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት መለኪያ የጽሑፍ መጠይቅና ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና የሚገኙት መረጃዎች በጥንቃቄ ተሰብስበው ከተተነተኑ በኋላ ከተገቢው ማጠቃለያና መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የተማሪዎቹ ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃትም ሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ ለየተላውጦዎቹ አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት ተሰልቷል፡፡ በመቀጠልም ለእያንዳንዱ ተላውጦ የጥናቱ ተሳታፊዎች ያገኙት ውጤት መደበኛ ልይይቶችን መሰረት በማድረግ ከየአማካይ ውጤቶቹ ምን ያህል በአማካይ እንደሚርቁ በማስላት በጣም ዝቅተኛ፣ ዝቅተኛ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛ እና በጣም ከፍተኛ በሚሉ ደረጃዎች እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡

በመቀጠል በተማሪዎች በማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት እና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽም የፒርስን የተዛምዶ ስሌት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ስሌቱ የተካሄደውም ሁለቱ ተላውጦዎች ያላቸው ግንኙነት በብትን ግራፍ (Scatterplot) ተሰርቶ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ተፈትሿል፡፡ በመሆኑም በተማሪዎች ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ዝምድና መኖር አለመኖሩ ለመፈተሽም የፒርስን የተዛምዶ ስሌት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ዝምድና ካላቸው የዝምድናቸውን እርከን ለማረጋገጥ ህብረ-ድኅረታዊ ትንተና ስሌት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

### 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ሁለት መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች አሉት፡፡

1. የመጀመሪያው ጥያቄ፡- “ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ አለውን?”
2. ሁለተኛው ጥያቄ ደግሞ፡- “ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል ነው?” የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስም በአንብቦ መረዳት ፈተና እና በማንበብ ተነሳሽነት የጽሁፍ መጠይቅ ከጥናቱ ተሳታፊዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በሚከተለው መንገድ ተተንትነው ውጤቶቹ ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱ ጥያቄ ““ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ አለውን?” የሚል ነበር፡፡ በመሆኑም የተለዋዋጮችን ተዛምዶ ለማወቅ የፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ቀመር በመጠቀም ውጤቱ ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

**ሰንጠረዥ፤4.1 የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በፒርሰን ተዛምዶ የመወሰኛ ቀመር**

| የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ንኡሳን ብልሃቶች (ተላውጦዎች) | የማንበብ ተነሳሽነት | ጉልህነት (P) |
|---|---|---|
| ጭንቀትን መቀነስ | .154 | 0.846 |
| ጥያቄ መጠየቅ | .178 | 0.642 |
| በትብብር መስራት | .645 | 0.701 |

በሰንጠረዥ 4.1 እንደሚታየው በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር መሠረት ሁሉም የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ የሆነ ጉልህ ተዛምዶ አሳይተዋል፡፡ በአንብቦ መረዳት ችሎታና ጭንቀትን በመቀነስ ንኡስ ብልሃት መካከል ያለው ተዛምዶ (r= 0.846፤ p< 0.01) መካከለኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም የሚያመላክተው በአንብቦ መረዳት ችሎታና ጭንቀትን በመቀነስ ንኡስ ብልሃት

መካከል አዎንታዊ መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡ ለዚህም ሁለቱ ተለዋዋጮች 84.6% ይጋራሉ፡፡ ይህም በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል አስተማማኝ ተዛምዶ መኖሩን ያመላክታል፡፡

በሌላኛው ማህበረ-ስሜታዊ ንኡስ ብልሃት(ጥያቄ በመጠየቅ) እና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ($r= 0.642$፤ $p< 0.01$) መካከለኛ ተዛምዶ መኖሩን አመላክቷል፡፡ ይህም የሚያሳየው ሁለቱ ተለዋዋጮች ጥያቄ መጠየቅና አንብቦ በመረዳት ችሎታ ንኡስ ብልሃት 64.2% ይጋራሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በትብብር መስራት በተሰኘው ንኡስ ብልሃትና አንብቦ በመረዳት ችሎታ መካከል ያለው ተዛምዶ ($r= 0.701$፤$p < 0.01$) መካከለኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ሁለቱ ተለዋዋጮች 70.1% ይጋራሉ፡፡ ይህም በሁለቱ ተለዋዋጮች መካከል አስተማማኝ ተዛምዶ መኖሩን ያመላክታል፡፡ በመሆኑም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ እንዳለው ያሳያል፡፡

የዚህ ጥናት ሁለተኛው ጥያቄ “ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል ነው?” የሚል ነበር፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በህብረ-ድህረታዊ ትንተና ስልት በሚከተለው ሰንጠረዥ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ፤ 4.2 ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻና ደረጃ በድኅረታዊ ትንተና

| ተላውጦዎች | የትጋርቶ መጠን (R square) | ድኅረታዊ መጣኝ (B) | መደበኛ ስህተት (Std. Erorr) | መደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ (Beta) | የቲ ዋጋ(t) | የጉልህነት ደረጃ (Sig) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጭንቀትን መቀነስ | 0.521 | 9.452 | 7.244 | 0.689 | 8.465 | 0.10 |
| ጥያቄ መጠየቅ | | 10.022 | 3.246 | 0.784 | 10.422 | 0.788 |
| በትብብር መስራት | | 10.54 | 7.677 | 0.745 | 10.564 | 0.549 |

ከሰንጠረዥ 4.2 እንደምንረዳው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ድርሻ ($r2= 0.521$፤ $p <0.01$) ሆኖ በመገኘቱ አስተማማኝ እንደሆነ ያሳያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የምንችለው ሶስቱም የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች (ጭንቀትን

መቀነስ፣ጥያቄ መጠየቅና በትብብር መስራት) በአንድ ላይ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የጎላ ድርሻ እንዳላቸው ያመላክታል። ከዚህም ባሻገር የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች በአንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ያላቸውን ቀጥተኛ ድርሻ ለማወቅ መደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ (B) ተሰልቶ የነጻ ተለዋዋጮች ድርሻ ቀጥሎ ቀርቧል።

የማህበረ-ስሜታዊ ንኡስ ብልሃት የሆነው ጭንቀትን መቀነስ አንብቦ ለመረዳት ችሎታ ያለው ድርሻ (B= 0.689፤ t= 8.465) አለው። ከዚህም መረዳት የምንችለው ተማሪዎች ለማንበብ ያለባቸውን ጭንቀት መቀነስ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማሳድግ መካከለኛ የሆነ ድርሻ ያለው መሆኑን ያሳያል። በተመሳሳይ መልኩ የማህበረ-ስሜታዊ ንኡስ ብልሃት የሆነው ጥያቄ መጠየቅ በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ የሚያበረክተው ድርሻ በስታትስቲክስ ተሰልቶ (B= 0.784፣ t= 10.422) በመሆኑ ጉልህ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ተማሪዎች ማንበብን ሲማሩ ጥያቄ መጠየቅ መቻላቸው ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መካከለኛ ድርሻ እንዳለው ያመላክታል። የመጨረሻው የማህበረ-ስሜታዊ ንኡስ ብልሃት የሆነው በትብብር መስራት አንብቦ ለመረዳት ችሎታ ያለው ድርሻ በስታትስቲክስ ሲሰላ (B= 0.745፣ t= 10.564) ያመለክታል። ከዚህም መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ማንበብን ሲማሩ በትብብር ቢሰሩ አንብቦ ለመረዳት ችሎታቸው መካከለኛ የሆነ ድርሻ እንደሚኖረው ይጠቁማል።

በአጠቃላይ በድኅረ ትንተናው እንደተገለጸው የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማሳደግ ረገድ ያላቸው የተጋርቶ መጠን $R^2$= 0.521 ወይም 52.1% መካከለኛ ነው። ከዚህ ውጤት በመነሳት ጭንቀትን መቀነስ፣ ጥያቄ መጠየቅና በትብብር መስራት በጋራ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት ላይ 52.1% መካከለኛ ድርሻ አላቸው።

ከማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች አንብቦ ለመረዳት ችሎታ በተናጠል ከፍተኛውን የተጋርቶ ድርሻ የያዘው ጥያቄ መጠየቅ ሲሆን 78.4% ያህል ነው። በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛውን የተጋርቶ ድርሻ የሚይዘው ደግሞ በትብብር መስራት ሲሆን 74.5% ያህል ነው። ሶስተኛው የማህበረ-ስሜታዊ ንኡስ ብልሃትና ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከለኛ ድርሻ የያዘው ጭንቀትን መቀነስ ነው። ይህ ንኡስ ብልሃትም ያለው የተጋርቶ ደርሻ 68.9% ያህል ነው።

በጥቅሉ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው በማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ የሆነ መካከለኛ ተዛምዶ ታይቷል። በተጨማሪም የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች የአንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻቸው ከፍተኛ መሆኑን አሳይቷል።

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነበር። በመሆኑም የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስም መረጃዎቹን በአንብቦ የመረዳት ፈተና እና በጽሑፍ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል። ጥናቱም ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ይዞ የተነሳ ሲሆን የመጀመሪያው ጥያቄ "ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ አለውን?" የሚል ነበር። ይህንን ጥያቄ ለመመለስም መረጃው በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር ተፈትሾ ተተንትኖ ቀርቧል። በመሆኑም መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት እንዳሳየውም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር መካከለኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል።

ሌላው የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄ "ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል ነው?" የሚል ነበር። ይህንን ጥያቄም ለመመለስ መረጃው በህበረ-ድህረታዊ ትንተና ስልት ተተንትኖ ቀርቧል። ከተገኘው ውጤትም በመነሳት የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች (ጭንቀትን መቀነስ፣ጥያቄ መጠየቅና በትብብር መስራት) ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት መካከለኛ ድርሻ እንዳላቸው አመላክቷል።

በመሆኑም የዚህ ጥናት ውጤት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ አለው ካሉት ከDoki & Katbelen (1999)፣ ከRutman (1994)፣ ከOxford & Borstok (1995) እና ከBoakye (2012) የጥናት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ሲሆን ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ የለውም ካሉት ከChoi (2011) እና ከGrebe & Stoller (2002) የጥናት ውጤት ጋር ደግሞ ይቃረናል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነበር፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ከዚህ ቀጥለው ለቀረቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሞከረ ነበር፡፡

1. ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ አለውን?
2. ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል ነው? የሚሉት ነበሩ፡፡

ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎችም ምላሽ ለማግኘት የጥናቱን ተሳታፊዎች በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በእሉ ገላን ወረዳ ከሚገኙት ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የኦዳ ብሲል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አመቺ የንሞና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል፡፡ በኦዳ ብሲል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በአምስት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የተመደቡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ ሲሆን የአስረኛ (D) ክፍል ተማሪዎችን በቀላል የዕጣ ንሞና ስልት በመምረጥ በድምሩ 80 ተማሪዎች የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ተመርጠዋል፡፡ ከዚያም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተዘጋጅተው መረጃዎቹ በተገቢው መልኩ ከተሰበሰቡ በኋላ ትንታኔና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ጥናቱ በዐይነቱ መጠናዊ፣ በንድፉ ደግሞ ተዛምዷዊ የጥናት ዘዴን በመከተል ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ለጥናቱ የዋሉት መረጃዎችም የተሰበሰቡት በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ ሲሆን መረጃ መሰብሰቢያዎቹ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት ከመዋላቸው አስቀድሞ በጥናቱ አማካሪ አማካኝነት ተገምግመው የሚሻሻሉትን በማሻሻል የሚወገዱትን በማስወገድ በድጋሜ ተዘጋጅተዋል፡፡ ከዚያም ቅድመ ጥናት ፍተሻ (Pilot Study) በማድረግ በተገኘው ውጤት መነሻነት ተገቢውን እርምት በማድረግ ለዋናው ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

ለጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎች ከተተነተኑ በኋላ እንደ ጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች እየታዩ በ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ቀመር ተተንትነው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃቶች (ጭንቀትን መቀነስ፣ ጥያቄ መጠየቅና በትብብር መስራት) አንድ ላይ ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር መካከለኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ በመሆኑም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃቶች ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር መካከለኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳላቸው ያመላክታል፡፡

በሌላ በኩል ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃቶች (ጭንቀትን መቀነስ፣ ጥያቄ መጠየቅና በትብብር መስራት) ከአንብቦ የመረዳት ችሎታጋር ያላቸው የተጋርቶ መጠን በህብረ-ድኅረታዊ ትንተና ስሌት ተሰልቶ ተዛምዶው 52.1% ሆኖ በመገኘቱ መካከለኛ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር መካከለኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳላቸው አመላክቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበትና የሚታዩባቸውን የአንብቦ መረዳት ችግሮቻቸውን ለመቀነስ ከሚያግዙ መንገዶች መካከል አንዱ ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃታቸውን ከፍ እንዲያደርጉ ማገዝ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ውጤትም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መነሻ በማድረግ ቀጥሎ ከሚከተለው የመደምደሚያ ሀሳብ ላይ ተደርሷል፡፡

ለጥናቱ ተሳታፊ እንዲሆኑ የተመረጡት ተማሪዎች ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃታቸው ከአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ጋር አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ በዚህም ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃታቸው ከፍ ሲል አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውም በዚያው ልክ እንደሚጨምር በጥናቱ ውጤት ተመላክቷል፡፡ ይህ ውጤት ሊገኝ የቻለበት ምክንያት የተማሪዎች ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እንዲጎለብት ስለተደረገ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶ ያለው መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማስተማር በትክክል ተግባራዊ ቢደረግ አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል፡፡

## 5.3 አስተያየት

አንብቦ መረዳት የፅሁፍን የመዋቅር አይነት ማወቅ፣ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ብልሃቶችን መረዳት፣ ዳራዊ ዕውቀትን መጠቀም፣ የፀሃፊውን ዳራ ማወቅንና የማህበረሰቡን ማህበረ-ባህላዊ አውድን ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚጠይቅ ውስብስብና አዕምሯዊ የሆነ ሂደት በመሆኑ ለመማር አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸውን ፅሁፎች አንብቦ ለመረዳት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃቶችንና አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ ስልቶችን ማስተማርና ማለማመድም ያስፈልጋል፡፡ ሊማሯቸውና ሊለማመዷቸው ከሚገቡ ብልሃቶች መካከልም በዚህ ጥናት የተፈተሸው ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር መካከለኛ የሆነ ተዛመዶ እንዳለው አሳይቷል፡፡

በጥናቱ የተረጋገጠውን ግኝት ተግባራዊ ለማድረግና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል በጥናቱ የተገኘውን ውጤትና መደምደሚያ መነሻ በማድረግ የሚከተሉት አስተያየቶችና ተጨማሪ የምርምር አቅጣጫዎች ተጠቁመዋል፡፡ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም፡-

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሻሻል በማስተማሪያ ዘዴያቸው ውስጥ ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትን ተጠቅመው ማንበብን ቢያስተምሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ላይ መካከለኛ የሆነ መሻሻል ያያሉ፡፡
2. ለተማሪዎች ስለማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ግንዛቤ ማስጨበጥና ማንበብን ሲማሩ ለብልሃቱ በሚመች መልኩ መተግብር ተገቢ ነው፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ስርዓተ-ትምህርት ባለሙያዎችና የመማሪያ መፅሃፍ አዘጋጆች አንብቦ ለመረዳት የሚያስችሉ መለማመጃ ተግባራትን ከግምት ውስጥ አስገብተው ቢያዘጋጁ ለተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮችን ሊቀንሱ ይችላሉ፡፡

ከዚህም ባሻገር በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ወደፊት ትኩረት ተደርጎባቸው ቢጠኑ ተብለው በአጥኚው የተጠቆሙ የጥናት አቅጣጫዎች፡-

1. ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ አዎንታዊ እንዲሆን የሚያደርጉ ሌሎች ተላውጦዎች (ሌሎች የማህበረ-ስሜታዊ ንኡሳን ብልሃቶች) ተካተው ቢታዩ ተገቢ ነው፡፡

2. ይህ ጥናት ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት እና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ በአንድ ትምህርት ቤትና በተወሰኑ ተሳታፊዎች የተፈተሸ በመሆኑ ወደፊት በርከት ባሉ ናሙናዎችና ሰፋ ያለ ጊዜ በመውሰድ በሌሎች ትምህርት ቤቶች ላይም ቢጠና ከዚህ የተለየ ወይንም የተሻለ ውጤት ሊገኝ ስለሚችል ቢሞከር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

# ዋቢዎች


ሰላማዊት አበበ፡፡ (2013)፡፡ *ማህበረ-ስሜታዊ የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፤በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያነት የቀረበ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡*

አማረ አበባው፡፡ (2001)፡፡ *ተራክቧዊ ማንበብን የማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብ የመረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅዕኖ፡- በአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተደረገጥናት፡፡ ባህርዳር፣ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡*

እንድሪስ አባይ፡፡ (2009)፡፡ *በቴክስት ውቅር ብልሃቶች በዐማርኛ ማንበብን መማር በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ተፅዕኖ፡- በስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት፤ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶስተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡*

ወይንሸት ግርማ፡፡ (2007*)፡፡ ማህበር ስሜታዊ ብልሃት የአማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ላይ አንብቦ የመረዳት ችሎታን እና የማንበብ ፍላጎትን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና፤ (በጫንጮ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት)፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፤ (ያልታተመ)፡፡*

ይሁኔ ገበየሁ፡፡ (2009)፡፡ *ልዕለአዕምሮ አንብቦ የመረዳት ዘዴ የማንበብ ክሂልን ለማጎልበት ያለው ሚና፡፡ ባህርዳር፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናት፡፡ (ያልታተመ)፡፡*

Aebersold,J. and Field, M. (1997).*From reading to reading teacher: Issues and strategies for second Language classrooms.* Cambridge, England: Cambridge university press.

Atkins, John, Halom Bante Yirga &Nuru Mohammed (1996). *Skills Development Methdology.* Addis Abeba: Addis Abeba University printing press.

Baker, L. and Brown, A. (1984). *Metacognitive Skills and Reading*. In P.D. Pearson, R.Kamil, &P Mosenthal (Eds.), Handbook of Reading Research (Vol.1, pp. 353-394). Mahwah, NJ: Lawrence Erlbaum Assoc.

Boakye, N, Y. (2012). *A Socio affective approach to improving student reading comprehension ability.* Athesis submitted in partial fulfillement of the requirments for the degree. University of Pretoria.

Brown, H.D. (1994). *Principle of language learning and teaching*. Englewood cliffs. Prints hall Regent.

Dick and Catbilen. (1991). *Essential Te aching Strategies*. *Teaching every Child to Read* University of Michinan.

Dornyei,Z. (2005). *The psychology of language learner individual difference in second language acquisitions.*

Choi, K. (2011). *Astudy on the effective of socio affective strategies on reading comprehension.* In korea university college students. From htt://www.paaljapan. org resources/ proceedi Ngs/ PAAL7/pdfs/05kyunghee. Pdf.

Ells, K. (1990). *Understanding second language acquisition.* Oxford: Oxford University Press.

Grebe, W.& Stoller, F. (2002). *Teaching and researching reading*. London: Person Education.

Goodman, K.S. (1994). *Learning about psycho-lingustics processes by analyzing oral reading.* Harvard education Review.

Griffiths,C.(2004). *Language learning strategies.Theory and research school foundation research*.cost.org

Graham, Richard, T. (1987). *Content Reading & the Reaction of meaning*. English teaching forum.

Hurd, S. and Lewis, T.(2008). *Languge learning strategeies in dependent setting.*

Johnson, D. S. (1978). *Naturally acquired learned helplessness: The relationship of school failure to achievement behavior, attributions, and self-concept*. Journal ofEducational Psychology, 73, 174—180.

Moorman, Gary, B. & Woo, D. (1990*). The Role of Purpose in Reading Instruction.* Jornal of The Reading Teacher, 43/7.486-493.

O'Malley,J. M, Chamot, A. U. Stewner-Manzanares, G., Kupper, L. J. and Russo, R.P. (1985). *Learning strategies used by Beginning and Intermediate ESL Students.* Language Learning, Vol. 35, No,1, pp 21-46.

O.Mally, C. and Chamot, A.U. (1990).*Learning Strategies in Second Language Acquisition*. Cambridgeuniversity Press.

Oxford,R. (1990). *Language Learning Strategies*: what every teacher should know. New York: New bury House Publisher.

Richards,J.C. (1978). *Understanding 2nd and foreign Language Learning Issues and Appro ches.* New bury hous publisher.

Rosenshine,B. Meister,C. & (1994). *Reciprocal teaching: A Review of the research*. Review of Educational Research, 64(4), 479-530.

Rubin, J. (1987).Learner Strategies: *Theoretical Assumption, Research History and Typology.* In A. Wenden and J. Rubin (eds) Learner Strategies in Language Learning. Englewood Cliffs, NJ. Prentice Hall.

Rutman, G. (1994). *Attitude Interested in Education*. Allfred Publishing.

Sabatini, J. Bruce, K. & Steinberg, J. (2013). SARA reading components tests, RISE form: Test design and technical adequacy (Research Report No. RR-13-08). Princeton, NJ:

Salam, K. (2013). *The effective of socio affective strategies on students' test anxiety across different genders.* Department of English language, Islamic azad university. From htt:/www. Academy. Peplisher. Com/index.php/tpls/article/view/tpls 0302269274.

Salovoara, H. (2005). *Achievement goals and cognitive learning strategy in dynamic context of Learning.*OULU University press.

Sheng.He.Ji. (2000). *A cognitive model for teaching Readingcomprension.*Forem, *38*(4), PP.12-15.

Stern, H.H. (1983). *Fundamental Concepts of Language Teaching.* Oxford University Press.

Williams, M. and Burden, R. (1997*). Psychology for language teachers a social constructivist approach.Cambridge; Cambridge University Press.*

Winter.(2004). *Language learning strategies in Foreign Language Learnig and Teaching. The* internet TESL journal, 6(8), forum http//iteesij.Org/Articles/.Hismanoglu. Strategies html.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና

## አጠቃላይ መመሪያ

ከዚህ በታች ሁለት ምንባቦች ቀርበዋል። ሁለቱም ምንባቦች አስር አስር የምርጫ ጥያቄዎችን አካተዋል። በድምሩ ሃያ ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆን ከስር ባሉት ንዑሳን መመሪያዎች መሰረት የጥያቄዎችን ትክክለኛ መልስ በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ ፃፍ/ፊ።

- ለፈተናው የተሰጠው ሰዓት 1:30
- እያንዳንዱ ጥያቄ አምስት ነጥብ ይዞ ድምሩ ከ100% ነው።
- የተፈተኑበት ቀን 17/08/2015 ዓ.ም
- ፈተናው የሚጀመርበት ሰዓት 8፡00 ሰዓት

የፈተናው ወረቀት 4 ገጽ መሆኑን አረጋግጡ።

**ምላሽ በመስጠት ስለተባበርከኝ/ሽኝ በጣም አመሰግናለሁ!!**

. ደገሉ ሮቢ

**ምንባብ አንድ**

ዘመን ይለዋወጣል የምንል የዋሆች መሆናችንን ሳስበው ይገርመኛል፡፡ የህይወታችንን አንድ ገጽታ ነካ የሚያደርግ አዲስ እውነታ በገጠመን ቁጥር "አይ ጊዜ! የማያሳየው የለ" እንላለን፡፡ ይህ አባባላችን አህያን "እንኳን ይህን ተሸከምሽ" ብሎ እንደማመስገን አለያም ለምን ይህን ተሸከምሽ ብሎ እንደመውቀስ ይቆጠራል፡፡ በመሰረቱ አህያ ወርቅም ሆነ አፈር የጫኗትን ነገር ትሸከማለች፤ የሚጭነውን ነገር መራጩ ሰው ነው፡፡ ዘመን የአህያ ጀርባ ነው፡፡ የሰጡትን ይቀበላል እንጂ በራሱ የሚለውጠው አንዳች ነገር የለውም፡፡ ሴኮንድ፣ ደቂቃ፣ ሰዓት፣ ቀን፣ ሳምንት፣ ወርና ዓመት ከጥንት ጀምሮ ነበሩ፤ እስከመጨረሻውም እንደነበሩ ይቆያሉ፡፡ ወቅቶች ሕጋቸውን ጠብቀው ይፈራረቃሉ፤ አንዱ ሌላውን ቀድሞ ወይም ስርዓቱን አፋልሶ የታየበት ጊዜ የለም፡፡

እርግጥ ነው ጊዜና ሰው ተነጣጥለው አይኖሩም፡፡ ግን ይህ ሲባል ዘመን አምላኪነት አዕምሯችን የፊጥኝ ጠፍሮ ሊያስረው አይገባም፡፡ ዘመን በገዛ ራሱ ተአምር አይፈጥርም፡፡ ለዘመን ትርጉም የሚሰጠው የሰው ልጅ ተግባር ነው፡፡ ዘመን አህያ ነው፡፡ የተጫነውን ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር ተሸክሞ ወደፊት ያዘግማል፡፡ ለነገ ማፈሪያም ሆነ መኩሪያ የሚሆን ተግባር የምናከናውነው እኛ ነን፡፡ የሰው ልጅ ከጣረ ጊዜ በጀርባዋ አዝላ ያሰበበት ጥሩ ስፍራ ልታደርሰው ትችላለች፡፡ ዘመን በተውኔት ማሳያ መድረክ ሊመሰልም ይችላል፡፡ መድረኩ ሁልጊዜ አለ፡፡ የሚለዋወጠውን ተውኔት ሁሉ እየተቀበለ ያሳያል፡፡ ታዲያ ተዋናዩ ጥሩ በተጫወተ ቁጥር መድረኩን ማመስገን ወይም ባበላሸ ቁጥር መኮነን ሞኝነት ነው፡፡ ሰው በገዛ አስተሳሰቡና ድርጊቱ የግሉንም ሆነ የማህበረሰቡን ህይወት ላሻሻለ ወይም ላበላሸ ዘመንን መመረቅ ወይም መርገም "በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ" ወይም "አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ" ያሰኛል፡፡

/የሺጥላ ኮከብ፣ እፍታ፣ 1991፤ ገጽ 15-21/

**መመሪያ አንድ፡- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች ተስማሚውን መልስ ምረጥ/ጭ።**

1. ከጥንዶቹ መካከል ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ዘመን - አህያለ. ሰው - አህያ   ሐ. ዘመን - መድረክ   መ. ጭነት - ሥራ

2. "ዘመን አምላኪነት አዕምሯችንን የፊጥኝ ጠፍሮ ሊያስረው አይገባም" ሲል ምን ማለቱ ነው? ሀ. በዘመን ማሳበባችንን መተው ይኖርብናል።

   ለ. ያለስራ መቀመጥ አይኖርብንም።

   ሐ. በአዲስ ዓመት ለስራ ታጥቀን መነሳት አለብን።

   መ. በዘመን መለወጫ በዓል የሚታየው ባዕድ አምልኮ መቅረት አለበት።

3. "አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የገባው የትኛውን ሀሳብ ለማጠናከር ነው?

   ሀ. ያልሰራው ሰው ሆኖ እያለ ዘመንን መውቀስ ተገቢ አይደለም።

   ለ. ማህበረሰቡ ጠንካራ ሰራተኛ ሆኖ እያለ ዘመንን መርገም አያስፈልግም።

   ሐ. አህያ ለተሸከመች ገበሬን ማመስገን ምን አመጣው።

   መ. ዘመን ባጠፋ ሰውን መውቀስ ተገቢ አይደለም።

4. ዘመንን ጥሩ ወይም መጥፎ የሚያሰኘው ምንድን ነው?

   ሀ. የዐውዳመት አከባበር   ሐ. የማህበረሰብ እምነት

   ለ. የወቅቶች መፈራረቅ   መ. የሰዎች ስራ

5. "አይጊዜ! የማያሳየው የለ" የሚለው አባባል ምንን ይገልጻል?

   ሀ. መገረምን   ለ. ምሬትን   ሐ. ትካዜን   መ. እልህን

6. "ተዋናዩ ጥሩ በተጫወተ ቁጥር ..." የሚለው የትኛውን ሀሳብ ይወክላል?

   ሀ. ተዋናዩ ጥሩ ተውኔት ባሰናዳ ቁጥር   ሐ. ዘመን በተለዋወጠ ቁጥር
   ለ. የሰው ልጅ መልካም ተግባር ባከናወነ ቁጥር   መ. የተውኔቱ ታዳሚዎች በተደሰቱ ቁጥር

7. ከምንባቡ ፍሬ ሀሳብ ጋር የሚስማማው አባባል የትኛው ነው?

   ሀ. የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም   ሐ. ስራ ለሰሪው እሾህ ላጣሪው

   ለ. ጊዜ ወርቅ ነው   መ. አትሩጥ አንጋጥ

8. በአህያ ጀርባ የተመሰለው ምንድን ነው?

   ሀ. ሰው   ለ. ተዋናይ   ሐ. ዘመን   መ. ጭነት

9. ትክክለኛ ሀሳብ የያዘው ዐረፍተነገር የትኛው ነው?
   ሀ. የሚለወጠው ሰው እንጅ ዘመን አይደለም፡፡
   ለ. የሚለወጠው ዘመን እንጅ ሰው አይደለም፡፡
   ሐ. የሚለወጠው አህያ እንጅ ጭነት አይደለም፡፡
   መ. የሚለወጠው መድረክ እንጅ ተውኔት አይደለም፡፡
10. "በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያስተላልፈው መልዕክት የሚያጎላው  የትኛውን ሀሳብ ነው?
   ሀ. ዘመኑ ባማረ ሰው ይመሰገናል፡፡ ሐ. ጨው በጣፈጠ ዘመን ይመሰገናል፡፡
   ለ. ሰው ባጠፋ ዘመን ይመሰገናል፡፡ መ. ሰው በሰራ ዘመን ይመሰገናል፡፡

**ምንባብ ሁለት**

ፈርጠም ያለ፣ የቀይ ሽንኩርት ቅርጽ መሳይ አፍንጫ ያለው፣ ዳጎብ ብሎ ቀላ ያለውን ከንፈሩን ሲገልጥ ነጫጭ ፍልጥ ጥርሶቹ የሚያማምሩና ከሽበላ ቁመናው ጋር የተስተካከለ አቋም ያለው ከሎ ሆራ ለየት ያለ ባህርይ ይታይበታል፡፡ ቁጥብነቱን፣ ጅንንነቱን፣ ጥርጣሬውንና ብቸኝነት መውደዱን ያዩ ጓደኞቹ "ነብሮ" ይሉታል-የዩኒቨርስቲ ጓደኞቹ፡፡ ቀልድና ቧልት ከጀመሩለት እንደቆሰለ ጎሽ በንዴት ጦፎ ይፎክራል፡፡ ከሰው ጋር ደጋግሞ እንደመጣላቱ ግን ሀይሉን ተማምኖ ተማቶ አያውቅም፡፡ ሁለቴ ሦስቴ ቃጥቶ-ቃጥቶ ምንም በማይገባው ቋንቋ አጉተምትሞ ዘወር ይላል፡፡ ታዲያ ብዙዎቹ አዳልጧቸው ቀልድ ቢጤ ጀማምረው በዚያ ፈርጣማ ጡንቻው በሰነዘረ ቁጥር ጠረመሰን እያሉ አንዴ ከተሳቀቁ "እርም" ብለው ይሸሹታል፡፡ ስለዚህ ምን እንደሚያበሸቀው፣ ያለፈው ህይወቱ ምን እንደሚመስል፣ ብቸኝነቱ ከመቼ ወዲህ እንደጀመረው ከፍቶ ማየት የጀመረ ሰው አልተገኘም፤ ግለቱም አላስቀረበም፡፡

የተማሪን ቀብ አውላቂ መምህራን በለመዱት ቧልት "ጢብ-ጢብ" ሊጫወቱበት ይዳዳቸውና እንደከለመዳሪ የሚነፋፋውን ከንፈሩንና እሳት ተፊ ትናንሽ አይኖቹን ሲያዩ በተለይም በአንቀሳቀሰው ቁጥር እንደአሎሎ የሚንከባለለውን ጡንቻውን ሲመለከቱ "በቸር አውለኝ" ብለው አቅጣጫቸውን ሲቀይሩ አመታት ተቆጠሩ፡፡ ... የልጅነት ጊዜው መጥፎ ትዝታ ጥርሱን አግጥጦ፣ ጥፍሩን በማሾል "የታባክ" ይለዋል፡፡ ይኸኔ እንደልጅነቱ ልጅ ይሆንና በጭንቀት እየተንቦራቸ ይርበተበታል፡፡ ትናንት ከገደል ውስጥ ወጥቷል፤ ዛሬ ግን ወደገደል ተገፍቶ ለመግባትና ለመሞት ዝግጁ አይደለም፡፡ እንግድህ ችግሩ ያለው

በትናንትና በዛሬ መካከል ነው፡፡ ልጅ ከነበረው ከሎና አሁን በአካልና በአዕምሮ ካደገው ከሎ አንድ ሽሽቱን ማቆም፤ አለበለዚያም "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ" እንዲሉ፣ በፍርሃት ላይ የጅቡን ፍርሃት እያከለ ወደኋላ ሳያይ የህይወትን ሩጫ መሸምጠጥ አለበት፡፡

(ፍቅረማርቆስ፣ ከቡስካ በስተጀርባ፣ 1987፣ ገጽ 13-15)

***መመሪያ ሁለት፡-*** ከጥያቄ 11-20 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ፡፡

11. "አዳልጧቸው" የሚለው ከአገባቡ አንጻር ለሚኖረው ፍቺ ተስማሚው የትኛው ነው?

    ሀ. አንሸራትቷቸው ሐ. አሟልጧቸው

    ለ. አምልጧቸው መ. አዳምጧቸው

12. "ቃጥቶ-ቃጥቶ፣ ጢብ-ጢብ" የተሰኙት ጥምር ቃላት ምን አይነት ሁኔታን ለማመልከት የገቡ ናቸው?

    ሀ. የድርጊት ተደጋጋሚነትን ለመግለጽ ሐ. ብዛትን ለመግለጽ

    ለ. ፍላጎትን ለመግለጽ መ. አይነትን ለመግለጽ

13. "በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ከገባበት አገባብና ከሚሰጠው ትርጉም አንጻር ምንን ለማመልከት የገባ ነው?

    ሀ. ዓይነትን ለመግለጽ ሐ. እየቀረ መሄድን

    ለ. እየረከሰ መሄድን መ. እየባሰበት መሄድን

14. "መሸምጠጥ አለበት" የሚለው የመደምደሚያ ዓረፍተነገር ምንን ያመለክታል?

    ሀ. መካድ አለበት ሐ. በፍጥነት መሮጥ አለበት

    ለ. መመልመል አለበት መ. መምጠጥ አለበት

15. "የተማሪ ቆብ አውላቂ መምህራን" ለሚለው የሚስማማው ትርጉም ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ የትኛው ነው?

    ሀ. ስነስርዓት የሚያስከብሩ መምህራን ሐ. ቆሌ የሚገፉ መምህራን

    ለ. ባርኔጣ የሚያወልቁ መምህራን መ. ቀልብ የሚስቡ መምህራን

16. የከሎ ሆራን ከንፈር በተመለከተ ከቀረቡት የተለያዩ አገላለፆች ውስጥ **የማይካተተው** የትኛው ነው? ሀ. እንደከለመዳሪ ይነፋል ሐ. ቀላ ያለ ነው

ለ. ለየት ያለ ነው መ. ዳጎስ ያለ ነው

17. በሁለተኛው አንቀጽ ካሉት ዘይቤያዊ አገላለፆች በሰውኛ ዘይቤነት የቀረበው ገላጭ ቃል ወይም ሀረግ የትኛው ነው?

ሀ. ከለመዳሪ ሐ. እሳት ተፊ

ለ. አሎሎ መ. ቆብ አውላቂ

18. ጡንቻውን ሲመለከቱ "በቸር አውለኝ" ብለው አቅጣጫቸውን ይቀይራሉ፤ የተባሉት እነማን ናቸው? ሀ. የከሎሆራ ያገሩ ልጆች ሐ. የከሎ ሆራ መምህራን

ለ. የከሎ ሆራ የዩኒቨርሲቲ ጓደኞቹ መ. ማጂራት መቺዎች

19. "እርም" ብለው ይሸሹታል ሲል ምን ማለት ነው?

ሀ. በድጋሚ አይሞክሩትም ሐ. "እርም" ካሉ በኋላ ይተፋሉ

ለ. ውጉዝ ያደርጉታል መ. እልም ብለው ይጠፋሉ

20. "ኩሩ" ለሚለው ቃል በአንቀጽ አንድ የተጠቀሰው ተመሳሳዩ ቃል የትኛው ነው?

ሀ. ነብሮ ለ. ፈርጣማ ሐ. ቁጥብ መ. ጅንን

**አባሪ (ለ). የጽሑፍ መጠይቅ**

**ውድ ተማሪዎች**! የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ የተማሪዎችን ማህበረ-ስሜታዊ ብልሃት ለመፈተሽ ለሚሰራው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም በመጠይቁ ለተካተቱት ጥያቄዎች የምትሰጧቸው እውነተኛ ምላሾች ለጥናቱ ከግብ መድረስ ወሳኝ በመሆናቸው በትክክል እንድትሞሉ እጠይቃለሁ፡፡

**ተማሪዎች ! መጠይቁን መሙላት ከመጀመራችሁ በፊት የሚከተሉትን መመሪያዎች በትክክል አንብቡ፡፡**

1. የመጠይቁ አሞላል ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ከተሰጡት ከ1 እስከ 4 ካሉት ቁጥሮች አንዱን ብቻ መርጦ (x) በቅንፉ ውስጥ ያለውን ምልክት በማድረግ ነው፡፡

2. በመጠይቁ ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ከ1 እስከ 4 ያሉት ቁጥሮች ቀጥሎ ያሉትን የውሳኔ ሀሳቦች የያዙ ናቸው፡፡

4 (በጣም እስማማለሁ)

3 (እስማማለሁ)

2 (አልስማማም)

1(በፍጹም አልስማማም) የሚሉ ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | በአማርኛ አንብቦ ለመረዳት | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 1 | ከባድና አመራማሪ መጻሕፍትን ማንበብ እወዳለሁ፡፡ | | | | |
| 2 | በማነባቸው መጻሕፍት በጥልቀት እንዳስብ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን ሳገኝ ደስ ይለኛል፡፡ | | | | |
| 3 | በሚመጣው ዓመት የተሻለ የማንበብ ስራ እንደምሰራ አውቃለሁ፡፡ | | | | |
| 4 | የሚያስደስተኝ መጻሕፍ ካገኘሁ ለማንበብ ከባድነቱ አያስጨንቀኝም፡፡ | | | | |
| 5 | ስለአዳዲስ ነገሮች (ጉዳዮች) ማንበብ እወዳለሁ፡፡ | | | | |
| 6 | ማንበብ ግዴታዬ ስለሆነ አነባለሁ፡፡ | | | | |
| 7 | መምህሬ የማንበብ ችሎታዬን እንዲያደንቁልኝ ማድረግ እወዳለሁ፡፡ | | | | |
| 8 | ጥሩ የማንበብ ችሎታ አለኝ፡፡ | | | | |
| 9 | የማንበብ ፈተና ውጤቴን ለማወቅ እጓጓለሁ፡፡ | | | | |
| 10 | በትርፍ ጊዜዬ ስለማከናውናቸው ነገሮች ይበልጥ ለማወቅ አነባለሁ፡፡ | | | | |
| 11 | በማንበብ ችሎታ ከሁሉም የተሻልኩ ምርጥ መሆን እፈልጋለሁ፡፡ | | | | |
| 12 | ማንበብ ግዴታዬ ስለሆነ አነባለሁ፡፡ | | | | |
| 13 | ለማንበብ ጥያቄዎች ከጓደኞቼ የበለጠ ትክክለኛ መልሶችን ለማግኘት እጥራለሁ፡፡ | | | | |
| 14 | በማንበብ ችሎታዬ ጥሩ መሻሻል እያሳየሁ እንደሆነ ወላጆቼ ወይም አሳዳጊዎቼ ብዙጊዜ ይገልጹልኛል፡፡ | | | | |
| 15 | የማንበብ ተግባሬን ከሌሎች ተማሪዎች ቀድሜ መጨረስ እወዳለሁ፡፡ | | | | |
| 16 | ጥሩ የማንበብ ችሎታ እንዳለኝ ጓደኞቼ አልፎአልፎ ይነግሩኛል፡፡ | | | | |
| 17 | ከቤተሰቦቼ ወይም ካሳዳጊዎቼ ጋር ብዙጊዜ ቤተመጻሕፍት እገባለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | የትምህርት ውጤቴን ለማሻሻል አነባለሁ፡፡ | | | | |
| 19 | ማንኛውንም የሚሰጠኝን የማንበብ ስራ መጨረስ ለእኔ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ | | | | |
| 20 | እኔና ጓደኞቼ የሚነበቡ ነገሮችን መቀያየር እንወዳለን፡፡ | | | | |
| 21 | ስለማነበው ነገር ለጓደኞቼ አወራላቸዋለሁ፡፡ | | | | |
| 22 | ለወንድሜ ወይም ለእህቴ ብዙጊዜ አነብላቸዋለሁ፡፡ | | | | |

ምንጭ፤ማስተዋልውበቱ (2011) ዊግፊልድና ጎትሪ (1997)Relations of children's motivation for reading to the amount of their reading. journal of educational psychology, 89(3), 420-32. Doi: 10.1037/0022-0663.89.3.420.በመጥቀስ ከተጠቀሙበት መጠይቅ ጥቂቶቹን በመውሰድ የተዘጋጀ፡፡

## አባሪ ሐ. የሙከራ ጥናቱ (Pilot Study) አንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት

| መለያ ኮድ | ከ 2 0 | መለያ ኮድ | ከ 1 0 0 | መለያ ኮድ | ከ 1 0 0 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 4 | 1 6 | 1 1 | 3 1 | 1 2 |
| 2 | 1 8 | 1 7 | 9 | 3 2 | 1 0 |
| 3 | 7 | 1 8 | 1 1 | 3 3 | 1 3 |
| 4 | 1 2 | 1 9 | 1 4 | 3 4 | 1 5 |
| 5 | 9 | 2 0 | 9 | 3 5 | 4 |
| 6 | 1 4 | 2 1 | 1 1 | 3 6 | 9 |
| 7 | 7 | 2 2 | 1 3 | 3 7 | 1 3 |
| 8 | 8 | 2 3 | 1 2 | 3 8 | 1 2 |
| 9 | 1 1 | 2 4 | 8 | 3 9 | 7 |
| 1 0 | 16 | 2 5 | 1 2 | 4 0 | 1 4 |
| 1 1 | 1 3 | 2 6 | 2 8 | | |
| 1 2 | 1 7 | 2 7 | 1 7 | | |
| 1 3 | 1 5 | 2 8 | 1 7 | | |
| 1 4 | 5 | 2 9 | 1 4 | | |
| 15 | 14 | 30 | 13 | | |

## አባሪ መ. የሙከራው ጥናት (Pilot Study) የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት

| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 |
| 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 |
| 3 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 |
| 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 |
| 5 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 |
| 6 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 1 | 3 |
| 7 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 |
| 8 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 |
| 9 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 10 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 |
| 11 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 |
| 12 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 13 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 |
| 14 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 |
| 15 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 |
| 16 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 |
| 17 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 |
| 18 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 |
| 19 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 |
| 20 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 |
| 21 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 |
| 22 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 23 | 4 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 1 |
| 24 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 25 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 26 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 27 | 2 | 4 | 2 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 28 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 29 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 30 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 |
| 31 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 |
| 32 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 |
| 33 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 34 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 |
| 35 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 |
| 36 | 3 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 |
| 37 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 |
| 38 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 |
| 39 | 1 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 2 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 |
| 40 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 |

## አባሪ ሠ. የዋናው ጥናት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት

| አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት | | አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት | |
|---|---|---|---|
| መለያ ኮድ | ውጤት (ከ20 ነጥብ) | መለያ ኮድ | ውጤት (ከ20 ነጥብ) |
| 1 | 14 | 59 | 18 |
| 2 | 18 | 60 | 12 |
| 3 | 12 | 61 | 8 |
| 4 | 14 | 62 | 14 |
| 5 | 9 | 63 | 9 |
| 6 | 17 | 64 | 13 |
| 7 | 8 | 65 | 17 |
| 8 | 10 | 66 | 14 |
| 9 | 12 | 67 | 18 |
| 10 | 15 | 68 | 16 |
| 11 | 17 | 69 | 14 |
| 12 | 13 | 70 | 17 |
| 13 | 11 | 71 | 15 |
| 14 | 7 | 72 | 17 |
| 15 | 14 | 73 | 16 |
| 16 | 11 | 74 | 17 |
| 17 | 14 | 75 | 11 |
| 18 | 17 | 76 | 16 |
| 19 | 8 | 77 | 18 |
| 20 | 12 | 78 | 16 |
| 21 | 14 | 79 | 16 |
| 22 | 11 | 80 | 14 |
| 23 | 6 | | |
| 24 | 19 | | |
| 25 | 11 | | |
| 26 | 18 | | |
| 27 | 12 | | |
| 28 | 12 | | |
| 29 | 13 | | |
| 30 | 5 | | |
| 31 | 9 | | |
| 32 | 4 | | |
| 33 | 13 | | |
| 34 | 15 | | |
| 35 | 17 | | |
| 36 | 18 | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | 7 | 1 | 2 |
| 3 | 8 | 1 | 0 |
| 3 | 9 | 1 | 1 |
| 4 | 0 | 9 | |
| 4 | 1 | 1 | 4 |
| 4 | 2 | 1 | 3 |
| 4 | 3 | 1 | 8 |
| 4 | 4 | 1 | 2 |
| 4 | 5 | 1 | 1 |
| 4 | 6 | 1 | 2 |
| 4 | 7 | 1 | 5 |
| 4 | 8 | 8 | |
| 4 | 9 | 1 | 5 |
| 5 | 0 | 9 | |
| 5 | 1 | 1 | 0 |
| 5 | 2 | 7 | |
| 5 | 3 | 1 | 3 |
| 5 | 4 | 1 | 3 |
| 5 | 5 | 1 | 2 |
| 5 | 6 | 1 | 2 |
| 5 | 7 | 1 | 4 |
| 5 | 8 | 1 | 2 |

## አባሪ ረ. የዋናው ጥናት የጽሑፍ መጠይቅ ውጤት

| ተ.ቁ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 |
| 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 |
| 5 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| 6 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 |
| 7 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 8 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 9 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 1 0 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 |
| 1 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 3 |
| 1 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 |
| 1 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| 1 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 1 5 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 1 6 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 |
| 1 7 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 1 8 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 1 9 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 2 0 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 |
| 2 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 |
| 2 2 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 |
| 2 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 2 4 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 |
| 2 5 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 |
| 2 6 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 2 7 | 2 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 2 8 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 |
| 2 9 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 |
| 3 0 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 |
| 3 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 3 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 3 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 |
| 3 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 35 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 36 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 |
| 37 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 |
| 38 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 39 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 40 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 |
| 41 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 42 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 |
| 43 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 44 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 45 | 4 | 3 | 4 | 3 | 5 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 46 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 |
| 47 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 |
| 48 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 |
| 49 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 50 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 51 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 |
| 52 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 53 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 54 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 55 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 56 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 57 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 |
| 58 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 |
| 59 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 60 | 3 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 61 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 62 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 |
| 63 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 64 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 65 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 66 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 67 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 68 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 69 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 70 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 |
| 7 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 |
| 7 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 7 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 7 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 7 6 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 |
| 7 7 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 7 8 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 |
| 7 9 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 8 0 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 |

### አባሪ ሰ. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ውጤት አስተማማኝነት

**Scale: ALL VARIABLES**

**Case Processing Summary**

| | | N | % |
|---|---|---|---|
| Cases | Valid | 80 | 100.0 |
| | Excluded[a] | 0 | .0 |
| | Total | 80 | 100.0 |

a. Listwise deletion based on all variables in the procedure.

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| .793 | 20 |

### አባሪ ሸ. የጽሑፍ መጠይቁ ውጤት አስተማማኝነት

**Scale: ALL VARIABLES**

**Case Processing Summary**

| | | N | % |
|---|---|---|---|
| Cases | Valid | 80 | 100.0 |
| | Excluded[a] | 0 | .0 |
| | Total | 80 | 100.0 |

a. Listwise deletion based on all variables in the procedure.

**Reliability Statistics**

| Cronbach's Alpha | N of Items |
|---|---|
| .965 | 22 |

### አባሪ ቀ. ከአንብቦ መረዳት ችሎታ የተገኘ የስታትስቲክስ ስሌት ውጤት

**One-Sample Statistics**

| | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|
| Reading comprehension | 80 | 74.52 | 7.964 | .7483 |

**One-Sample Test**

| | Test Value = 70 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | T | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | Lower | Upper |
| Reading comprehension | 7.686 | 79 | .000 | 6.52 | 5.09 | 6.94 |

## አባሪ በ. የማህበረ-ስሜታዊ ብልሃትና አንብቦ የመረዳትችሎታ ተዛምዶ በስታትስቲክ ስሌት

**Correlations**

| | | Reading self-efficancy Believes | Reading comprehension |
|---|---|---|---|
| Socio-Affective strategies | Pearson Correlation | 1 | .521** |
| | Sig. (2-tailed) | | .000 |
| | N | 80 | 80 |
| Reading comprehension | Pearson Correlation | .521** | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | |
| | N | 80 | 80 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed)

## አባሪ ተ. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ የስታትስቲክስ ስሌት ውጤት

**One-Sample Statistics**

| | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|
| Socio- Affective strategies | 80 | 76.64 | 5.92 | .711 |

**One-Sample Test**

| | Test Value = 70 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | t | df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | Lower | Upper |
| Reading socio Affective strategies | 14.77 | 79 | .000 | 9.74 | 8.56 | 11.84 |

## አባሪ ቸ. ከአንብቦ መረዳት ችሎታ የተገኘ የስታትስቲክ ስሌት ውጤት

**One-Sample Statistics**

| | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|
| Reading comprehension | 80 | 72.52 | 7.96 | .718 |

**One-Sample Test**

| | Test Value = 70 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | T | Df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | | | | | Lower | Upper |
| Reading comprehension | 7.66 | 79 | .000 | 5.52 | 5.09 | 7.94 |

## አባሪ ኀ. የአንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ተዛምዶ በስታትስቲክ ስሌት

**Correlations**

| | | Reading motivation | Reading comprehension |
|---|---|---|---|
| Reading Readibg motivation | Pearson Correlation | 1 | .521** |
| | Sig. (2-tailed) | | .000 |
| | N | 80 | 80 |
| Reading comprehension | Pearson Correlation | .521** | 1 |
| | Sig. (2-tailed) | .000 | |
| | N | 80 | 80 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).